የሀይደልበርግ ካተኪዝም

Heidelberg Catechism

Translated & Printed
by MERF Ethiopia 2011/2019

1. በሕይወትና በሞት የመጨረሻና ዋና ተስፋህ ምንድንነው?

እኔ በስጋየየና በነፍሴም ፣በዚህም ህይወት ሆነ በሞት፣ (1)የራሴ ሳልሆን ፣(2) የታማኙ አዳኜ ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ፣(3) እርሱ በክብር ደሙ (4) ለሀጢያቴ ሁሉ ሙሉ ዋጋ ከፍሎ፣(5) ከሰይጣን ሀይል ዋጅቶኛል፣(6) ስለሚጠብቀኝ(7) በሰማይ ካለው አባቴ ፈቃድ ውጪ ከራሴ ላይ አንዲት ቅንጣት ፀጉር አትወድቅም፣(8) በርግጥም ሁሉ ነገሮች ባንድነት ለድነቴ ይሰራሉ።(9) ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ የዘላለም ህይወር ወራሽ መሆኔን ያረጋግጥልኛል ፣(10) ከልቤ ፈቃደኛና ዝግጁ ሆኜ ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ እንድኖር ያደርገኛል።(11)

(1) ሮሜ 14÷7-9፡(2) 1ቆሮ 6÷19-20፡(3) 1ቆሮ 3÷23፤ቲቶ 2÷14።(4) ጴጥ 1÷18-19፡(5) 1ዮሐ 1÷7፤2÷2፡(6)ዮሀ 8÷34-36፤ዕብ 2÷14-15፤1ዮሀ 3÷8።(7) ዮሐ 6÷39-40፤10÷29-31፤ ሉቃስ 21÷16-18።(9) ሮሜ 8÷28።(10)ሮሜ 8÷15-16፤ 2ቆሮ1÷21-22፤5÷5፤ኤፌ1÷13-14።(11) ሮሜ 8÷14

2. በዚህ መጽናናት በደስታ እንድትኖርና እንድትሞት ልታውቅ የሚያስፈልጉህ ነገሮች ስንት ናቸው

ሦስት ነገሮች፤(1) አንደኛ፤የኃጥያቴን ታላቅነትና ከንቱነቴን ። (2) ሁለተኛ፤ከሀጥያቴና ከከንቱነቴ የተዋጀሁ መሆኔን።(3) ሶስተኛ፤ ለዚህ መዋጀት ምስጋና መስጠት እንደሚገባኝ ።(4)

(1)ሉቃስ 24÷46-47፤ሮሜ 7÷24-25፤1ኛ ቆሮ 6÷11፤ ቲቶ 3÷3-7።(2) ዮሐ9÷41፤15÷22፤ ሮሜ3÷9-10፤1ዮሐ 1÷10።(3) ዮሀ 17÷3፤ ሐሥ 4÷12፤10÷43፤ገላ3÷13። (4) ማቴ 5÷16፤ሮሜ 6÷13፤ኤፌ 5÷8-11፤ቆላ 3÷17፤ 1ጴጥ2÷9-12።

ክፍል አንድ
የጎጢያት እዳ
2ኛው ሰንበት

3. በኃጥያት የተጎሳቆልክና ምስኪን መሆንህን ከየት ታውቃለክ?

ከእግዚአብሄር ህግ። (1) (1) ሮሜ 3÷20፤7÷7።

4.የእግዚአብሄር ህግ ከእኛ ምን ይፈልጋል?

ክርስቶስ በማቴዎስ 22 ላይ ባጭሩ እንዲህ ብሎ አስተምሮናል፤ “ጌታ አምላክህን በፍፁም ልብህ በፍፁም ነፍስህን በፍፁም አሳብህን ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህቺ ናት። (1) ሁለተኛይቱ ይቺህን ትመስላለች፣እርሷም።ባንጀራህን እንደነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። (2) በእነዚህ በሁለቱ ትዛዛት ህጉም ሁሉ ነብያትም ትሰቅለዋለች። (3)

(1) ዘዳ 6÷5።(2) ዘሌ19÷18፤ ገላ 5÷14። (3) ሉቃስ 10÷27።

5. ይህንን ሁሉ በትክክል መጠበቅ ትችላለህን?

አልችልም። (1) እኔ በተፈጥሮዬ እግዚአብሄርንና ባልጀራዬን ለመጥላት ያዘነበልሁ ነኝና። (2)

(1) ሮሜ 3÷10-12፣23፤1ኛ ዮሀ 1÷8ና10። (2) ዘፍ 6÷5፤8÷21፤ኤር 17÷9፤ሮሜ 7÷23፤8÷7፤ ኤፌ2÷3፤ቲቶ2÷3።

3ኛ ሰንበት

6. እግዚአብሄር ሰውን እንደዚህ ክፉና ጠማማና ርኩስ አድርጎ ፈጠረውን? አልፈጠረውም። እግዚአብሄርስ ሰውን ጥሩ አድርጎ ነበር የፈጠረው፤(1) ለራሱ መልክና ምስል ፈጥረው፤(2) ያም የጽድቅና በእውነተኛ ቅድስና፣(3) ያም ደግሞ እግዚአብሄርን ፈጣሪንም በትክክል ያውቅ ዘንድ፤(4) ከልቡ ያፈቅረው ዘንድና ከእሱ ጋር በዘላለም ደስታ ይኖር ዘንድ፣ያመሰግነውና ያከብረው ዘንድ።(5)

(1) ዘፍ 1÷31፤(2) ዘፍ 1÷26-27።(3)ኤፌ4÷24፤2ቆሮ3÷18።
(4)ቆላ 3÷10። (5) መዝ 8።

7. ታዲያ ይህ ከተበላሸው የሰው ባህሪይ ከየት መጣ?

ከመጀመሪያወቹ ወላጆቻችን፣ከአዳምና ከሄዋን በገነት ውሥጥ ከፈፀሙት አለመታዘዝ፤(1) ከዚያም የተነሳ ባህሪያችን ተበላሸ፤ (2) በኀጢአትን ተፀንሰን በኀጥያት ተወልደን።(3)

(1) ዘፍ3። (2) ሮሜ 5÷12፤18-19።(3) መዝ 14÷2-3፤ 51÷5።

8. **እንግዲህ በኀጥያት ፈጽሞ ርኩስ ሆነን፣ምንም መልካም ነገርን ማድረግ የተሳነንና ሁልጊዜ ወደክፋት ያዘነበልን ነን?**

አዎ።(1) በእግዚአብሄር መንፈስ ዳግም ካልተወለድን በስተቀር። (2)

ዘፍ 6÷5፤8÷21፤ኢዮብ 14÷4፤ኢሳ 53÷6፤ኤር17÷9፤ ዮሀ3÷6፤ሮሜ7÷18።(2) ዮሐ 3÷3-5።

4ኛው ሰንበት

9. **እንግዲህ ሰው ሊፈጽመው የማይችለውን ሕግ እንዲታዘዝ መጠበቅ የሚችል አድርጎ ሰውን ፈጥሮ ነበር፤ (1) ነግር ግን በሰይጣን ተነሳስቶ፣ (2) በራሱን እንቢተኝነትና አለመታዘዝ፣(3) ራሱንና ዘሩን በሙሉ ይህን የመታዘዝ ጎይል እንዲያጡ ለማድረግ በቃ።(4)**

(1) ዘፍ1÷31፤ኤፌ4÷24።(2) ዘፍ 3÷13፤ዮሐ8÷44፤1 ጢሞ 2÷13-14።(3) ዘፍ 3÷6።(4) ሮሜ 5÷12፤18-19።

10. **እግዚአብሄር ይህን አለመታዘዝና መውደቅ ሳይቀጣ ዝም ብሎ ያልፈዋልን?**

በፍፀም አያልፈውም፤(1) እግዚአብሄር በተፈጥሮ በወረስነውም፣ በተግባር በምንፈጽመው ኃጢአት እጅግ ይፀየፋል፤ ስለዚህ በዚህ ህይወትና በዘላለሙ ህይወት ኃጢአትን በጽድቅ ፍርድ ይቀጣል። (2) በቃሉም "የዚህን ህግ ቃሎች ያደርጉ ዘንድ የማይፀና ርጉም ይሁን "ብሏል። (3)

(1) ዕብ 9÷27(2) ዘዕ 34÷7፤መዝ5÷4-6፤7÷10ነህ1÷2፤ ማቴ25÷41፤ሮሜ1÷18፤5÷12፤ ኤፌ5÷6።(3) ዘዳ 27÷26፤ገላ 3÷10።

11.**እግዚአብሄር ማህሪስ ነውን?**

አዎ፤ በርግጥም እግዚአብሄር ማሃሪ ነው፤(1) ደግሞም ፃዲቅ ስለሆነ፣ ሀጢአትን የእግዚአብሄርን ክብር ይጋፋልና፣ ኃጢአትን ተገቢውን ፍርድ እንዲቀበል አሏል፤ ያም ፈርድ ለዘላለም በነፍስም በስጋም መሰቃየት ነው። (3)

(1) ዘዳ 20÷6፤ 34÷6-7፤መዝ 103÷8-9።(2) ዘዕ 2÷5፤ 34÷7፤ዘዳ7÷9-11፤መዝ 5÷4-6፤2ቆሮ 6÷14-16፤ዕብ 10÷30-31፤31 ራዕይ 14÷11።(3) ማቴ 25÷25-46። ክፍል ሁለት፤ጸጋ (ጥ.12-87)

ክፍል ሁለት
ነጻነታችን
5ኛው ሰንበት

12. እንግዲህ በእግዚአብሔር ጻድቅ ፍርድ በዚህ ሕይወትና በሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ የገባን ሆነን ከተገኘን፣ይህን ፍርድ እንዴት እናመልጣለን፤ በእግዚአብሔር እንዴት እንደገና ተቀባይነትንስ እናገኛለን?

ጻድቅ ፍርድ እንዲፈጸም እግዚአብሔር አሏል፤(1) ስለዚህ አንድም በራሳችን ወይም በሌላ የተፈረደብንን የእግዚአብሔርን የፍርድ እዳ መክፈል አለብን። (2)

(1)ዘጸ 20÷5፤ 23÷7፤ ሮሜ 2÷1-11።(2) ኢሳ 53÷11፤ ሮሜ 8÷3-4።

13. እኛ እራሳችን በራሳችን ይህን የፍርድ እዳ መክፈል እንችላለን?

በፍፁም እንችልም፤ እንዲያውም በየቀኑ የፍርድ እዳችንን እየጨመርን ነው። (1)

(1)ኢዮብ 9÷2-3፤ 15÷15-16፤ መዝ 130÷3 ማቴ 6÷12፤ ሮሜ 2÷4-5።

14. ማንኛውም ተራ የሆነ ፍጡር የፍርዳችንን እዳ ሊሸከምልንና ሊያስወግድልን ይችላል?

በፍጹም፤ በመጀመሪያ ሰው ለፈጸመው በደል አይቀጣም ማንኛውንም ሌላ ፍጡር እግዚአብሔር አይቀጣም፤ (1)በተጨማሪም ማንኛውም አይነት ተራ ፍጡር የእግዚአብሔርን የዘላለም ኩነኔ ሊሸከምናሌሎችን ከዚህ ፍርድ ሊዋጅ አይችልም። (2)

(1) ሕዝ 18÷4÷፤20 ዕብ 2÷14-18። (2) መዝ 130÷3፤ነህ 1÷6።15 እንግዲያ ምን ዓይነት መካከለኛ ወይም ቤዛ ያስፈልገናል? እውነተኛ የሆነና (1) ጻድቅ የሆነ ሰው (2) ደግሞም ከፍጡሮች ሁሉ በላይ ኃይል የሆነ፣ማለትም ራሱ እውነተኛ አምላክ የሆነ።(3)

(2) (1) ቆሮ 15÷21-22፤25-26፤ዕብ 2÷17። (2) ኢሳ 53÷11 ኤር 13÷16፤2ቆሮ 5÷21፤ዕብ 7÷26።(3) ኢሳ 7÷14፤9÷6፤ኤር23÷6፤ዮሐ1÷1፤ሮሜ8÷3-4፤ ዕብ 7÷15-16።

6ኛው ሰንበት

16 እውነተኛ ጻድቅ ሰው መሆን ለምን አስፈለገ?

ምክንያቱም የእግዚአብሄር የጻድቅ ፍርድ ለኃጥያት የቤዛነት ዋጋ የሚከፍል የኃጥያትሰሪው ባህሪይ መሆን ስላለበት ነው ፤(1) ነገር ግን እራሱ ራሱ ንጥያተኛ ሆነ ለሌሎች ለሀጥያት የቤዛነት ዋጋ መክፈል አይችልም።(2)

(1) ሮሜ 5÷12 15፤1ቆሮ 15÷21 ዕብ 2÷14-16። (2) ኢሳ 53÷3 5፤ዕብ 7÷26-27፤1ጴጥ 3÷18።

17. ደግሞስ ለምን እውነተኛ አምላክ መሆን አስፈለገው

የእግዚአብሄር ቁጣ በመለኮታዊ ሀይሉና (1) በሰውነት ባህሪው መሸከም እንዲችል(2) በዚያም ጻድቅና ሕይወት እንዲያስገኝልንና (3) መልሶ እንዲሰጠን።(4) (1) ኢሳ 9÷5።(2) ዘዳ 4÷24 ዕብ ኢሳ 53÷8 መዝ 130÷3፤ነህ 1÷6 ሀሥ 2÷24። (3) ዮሐ 3÷16 ሐሥ 20÷28። (4) ኢሳ 53÷5፣ 2ቆሮ 5÷21፤ 1ዮሐ 1÷2።

18. አሁን እንግዲህ መካከለኛ ሊሆን የሚችል በእንድ አካል (እኔነት) እውነተኛ አምላክና እንዲሁም እውነተኛ ጻድቅ የሆነ ሰው ማነው?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 910 ሙሉ ቤዛነትና ጻድቅን እንዲሁ በነፃ እንዲያስገኝልን የተሰጠን እርሱ ነው።(2) (1) ማቴ 1÷21-23፤ሉቃስ 2÷11፣1ጢሞ 2÷5፤3÷16። (2) ሐሥ 4÷12 ቀቆር 1÷30።

19. ይህን እንዴት ልናውቅ ቻልን?

ራሱ እግዚአብሄር በገነት ከገለጠልን ከቅዱስ ወንጌል በብሉይ በቅዱሳን አባቶችና (2) ነቢያት (3) የታወጀው ፣በብሉይ ኪዳን መስዋቶችና ስርአቶች አሰቀድሞ በምሳሌ የተመሰለው (4) በኃላም በተወደደው ልጅ የተፈፀመው ።(5) (1) ዘፍ 3÷15። (2) ዘፍ 12÷3፤22÷18፤49÷10-11። (3) ኢሳ 53፤፤ኤር 23÷5-6፤ ሚክ 7÷18-20 ሐሥ 3÷22 -24፤10÷43፤ሮሜ 1÷2፤ዕብ 1÷1። (4) ዘሌ 1÷7፤ዮሐ 5÷46፤ዕብ10÷10።(5) 10÷4፤ገላ 4-5፤ቆላ 2÷17፤ዕብ 10÷1።

7ኛው ሰንበት

20. ሁሉም ሰዎች በአዳም እንደጠፉ፣በክርስቶስ ድነዋልን አልዳኑም። የ ሚድኑት በእውነተኛ እምነት በክርስቶስ ውስጥ የተተከሉትና የእርሱን የማዳን ተግባር ውጤቶች ተቀበሉ ብቻ ናቸው። (1)

(1) መዝ 2÷12፤ማቴ 7÷14፤ዮሐ 1÷12-13፤3÷16፣18፤ ሮሜ 11÷16-21፤1ቆሮ 15÷22፤ ዕብ 4÷2-3፤10÷39

21. እውነተኛ እምነት ምንድነው

እውነተኛ እምነት፤እግዚአብሄር በቃሉ የገለጠውን በቃሉ የገለጠውን እውነት ነው ብየየ መቀበል ብቻ ሳይሆን ፤(1) ደግሞም በወንጌል አማካኝነት መንፈስ ቅዱስ በልቤ የሚሰራው መታመን በቃሉ ላይ ከልብ መደገፍ፣(2፣3፣) የኀጢያት ስርየት፣ የዘላለም ጽድቅና ድነት ለሌሎች ብቻ ሳይሆን፣ለእኔም ደግሞ በእግዚአብሄር በነፃ እንደሚሰጡ ከልብ በሆነ እምነት ማረፍ።(5፣ 6፣7)

(1) ዮሐ 17÷3፤ዕብ 11÷1-3፤የዕ 1÷6 2÷19።(2) ሮሜ 4÷16-21፤5÷1 10÷10፤ ዕብ 4÷16።(3) 2ቆሮ 4÷13፤ፊል 1÷19፣29።(4) ሐሥ 16÷4፤ሮሜ 1÷16፤ 10÷17፤ቆሮ 1÷21። (5) ገላ 2÷20። (6) ሮሜ 1÷17፤ዕብ 10÷10፤11÷1-2።(7) ሐሥ 10÷43፤ ሮሜ 3÷20-26፤ገላ 2÷÷16፤ ኤፌ 2÷16፤ ኤፌ 2÷7-10።

22. ታዲያስ እንግዲህ ለክርስቲያን ማመን ማለት ምንድን ነው

በወንጌል በተስፋ ቃልሰጠንን ሁሉ፣(1) ያም ያለጥርጥር ዓለም ዓቀፍ የሆነው የክርስትና እምነት በአጭሩ እንደሚከተለው ያስቀመጠልንን፡፡

(1) ማቴ 28÷19-20፤ዮሐ 20÷30-31፤2ጢሞ 3÷15፤ 2ጴጥ 1÷21።

ሐዋርያዊ የእምነት መግለጫ (የጸሎት ሃይማኖት)

23. እነዚህን የእምነትአንቀጾች ምንድናቸው

እኔ ሁሉን በሚችል ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በእግዚአብሄር አብ አምናለሁ፡፡ ደግሞም በአንድ ልጅ ፤በመንፈስ ቅዱስ በተሰነፀ፣ከድንግል ማርያም በተወለደ፣በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራን በተቀበለ ፤ በተሰቀለ በሞተ፣በተቀበረ፣ወደ ሲዖል በወረደ ፣በሶስተኛውም ቀን ከሙታን በተነሳ፣ወደ ሰማይ በወጣ፣ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሄር አብ ቀኝ በተቀመጠ፣ በሕያዋንናበሙታን ሊፈርድ ከዚያም በሚመለስ በጌታችን በኢየሱስ ክርቶስ አምናለሁ ፡፡ ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ፣ በአንዲት ቅድስት ሀዋርያት ቤተክርስቲያን፣በቅዱሳን በአንድነት በኃጢያት ሥርየት፣በስጋና ትንሳኤ በዘላለም ሕይወት አምናለሁ፡ ፡ አሜን፡፡

ሥላሴ

8ኛው ሰንበት

24. እነዚህ አንቀጾች የተከፋፈሉት እንዴት ነው

በሦስት ተከፋፍለዋል፡፡ የመጀመሪያው የእግዚአብሄር አብና መፈጠራችን ነው፣ሦስተኛው እግዚአብሄር ፣መንፈስ ቅዱሽናችንና፡፡(1) (1) 1ጴጥ 1÷2

25. አንድ የመለኮት ባሕሪይ ብቻ ስላለ ፣ (1) ለምን ታደያ ስለ ሦስት አካላት ትናገራለህ

ምክንያቱም እግዚአብሄር እንደዚህ አድርጎ ራሱን በቃሉ ስለገለጠ ነው። (2) እነዚህ ሦስቱ አካላት አንድ አውነተኛና ዘላለማዊ አምላክ ናቸው።

(1) ዘዳ 6÷4፤ኢሳ 44÷6 45 ÷5 1ቆሮ 8÷4-6።(2) ዘፍ 12-3 መዝ ኢሳ 61÷1 63÷8-10 ማቴ 3÷16-17 28÷18-19 ሉቃስ 4÷18 ዮሀ 14÷26 15÷26 2ቆሮ 13÷14 ገላ 4፤6 ቲቶ 3፡5-6

ስለ እግዚአብሄር አብና ስለ መፈጠራችን

9ኛው ሰንበት

26. እኔ ሁሉን በሚችል፣ሰማይና ምድርን በፈጠረ እግዚአብሄር አብ አምናለሁ ስትል የምታምነው ምንድን ነው ዘላለማዊ የጌታች የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፣ከምንም ሰማይንና ምድርን እንዲሁም በውስጣቸው ያሉትና ሁሉ የፈጠረ፣(1) በዘላለማዊ ምክሩ ሁሉን የሚደግፍና የሚያስተዳድር ፣(2) ለልጁ ለክርስቶስ ሲል የእኔ አምላክና አባት ነው (3) ከእርሱም ለነፍሴና ለስጋዬ የሚያስፈልገኝ ሁሉ (4) እንደሚሰጠኝ አምናለሁ። በተጨማሪም በዚህ መከራ በሞላበት ህይወት ውስጥ ምንም አይነት ክፉ ነገር ቢልክብኝ ሁሉን ለእኔ መልካም እንዲሆን ያደርጋል፣(5) እርሱ ሁሉን ቻይ አምላክ ስለሆነ ያንን ማድረግ ይቻለዋል (6) ታማኝ አባቴ ስለሆነም ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ ነውና (7)

(1) 1-2 ዘጸ 20÷11፤ኢዮብ 38-39፤መዝ 33÷6፤ኢሳ 44፡24፤ ህዝ 4÷24፤14÷15፤ቆላ 1÷16 ዕብ 11÷3።(2) መዝ 104÷2-5 27-30፤ማቴ 6÷30 10÷29-30 ህስ 1÷24-25 ኤፍ ቫ1÷11 ዕብ 1÷3 (3) ማቲ 6÷8 ዮሐ 1÷12-13፤ሮሜ 8÷15-16 ገላ 4÷4-7 ኤፌ 1÷5፤3÷14-16(4) ምዝ 55÷22 90÷1-2 ማቴ 6÷25-26 ሉቃስ 12÷22-31(5) ሐሥ 7÷27-28 ሮሜ 8÷28(6) ዘፍ 18÷14፤ሮሜ 8÷31-39፤ 10÷12(7) ዝን 23÷19፤ማቴ 6÷32-33፤7÷9-11።

መግቦተ እግዚአብሄር

10ኛው ሰንበተ

27. ሁሉን ቻዩና በሁሉ ሥፍራ የሚገኘው ኃያሉ አምላክ፣ (1) ሰማይንና ምድርን እንዲሁም በውስጣቸው የሚገኙትን ፍጥረቶች ሁሉ በኃያሉ እጆቹ እየደገፈ (2) ያተዳድራቸዋል፤ እጽዋትን፣ ዝናብንና ፀሐይን(3) የብላቲና የደረቀ ዘመናን፣ ምግብንና ውሃ (4) ጤንነትንና ሕመምን፣ (5) ብልጽግናንና ድህነትን (6) አሥ ሁሉንም ነገሮች የሚቆጣጠራቸው አጋጣሚ (ቻንስ) ሳይሆን፣ (7) አባታዊ እጆቹ ናቸው። (8
(1)ኤር 23÷23-24፣ ሐሥ17÷24-28 ዕብ 1÷3 3 ኤር 5÷24፡ ፡ (4) ሐሥ ÷15-17 (5) የሐ 9÷3። (6)ኢዮብ 1÷21 መዝ 103÷፤ ምሳሌ 22÷1፣ ሮሜ 53÷5 (7) ምሳሌ 1÷33። (8) ማቴ 10÷29 ኤፌ 1÷1
28. እግዚአብሔር ፈጣሪ መሆኑንና ሁሉንም ነገር በቅዱስ አስተዳደሩ እየደገፈ መሆኑን ማወቅ ምን ይጠቅማል?

በችግራችን ጊዜ እንድንታገስ፣ (1) በመልካም ጊዜያችን እንድናመሰግን፣ (2) ስለወደፊቱም ምንም ፍጡር ከፍቅሩ ሊለየን እንደማይችል በታማኙ አባታችን በእግዚአብሔር እንድንተማመን፣ (3) ምክንያቱም ሁሉም ፍጡሮች በእጁ ስለሆኑ፣ ያለ እርሱ ፈቃድ መንቀሳቀስ እንኳን አይችሉምና። (4)
(1)ኢዮብ 1÷21-22፣ መዝ 39÷10፣ ሮሜ 5÷3 ያዕ 1÷3።(2) ዘዳ 8÷10 ተሰ 5÷18።(3) መዝ 55÷22፣ ሮሜ 5÷3-5፣ 8÷35፣ 38-39። (4) ኢዮብ 1÷12፤ 2÷6፤ መዝ 71÷7፤ ምሳሌ 21÷1፤ ሐሥ 17÷24፤ 2ቆሮ 1÷10።

እግዚአብሔር ወልድና መዋጀታችን

11ኛው ሰንበት

29. የእግዚአብሔር ልጅ ለምን «ኢየሱስ» ማለትም፣ አዳኝ ለምን ተባለ?

ከኃጢያታን ሁሉ ስለሚያድነን፣ (1) እና በሌላ መንገድ መዳኛ ስለሌለ፣ ለመዳን በሌላ መንገድ መሻት ወይም መሞከር የለብንም ማት ነው።(2)
(1)ማቴ 1÷21፤ ዕብ 7÷25። (2) ኢሳ 43÷11፤ ሉቃስ 2÷10-11፤ ዩሐ 15÷4-5 ሐሥ 4÷11-12፤ 1ጢሞ 2÷5

30. መዳንና ደኃንነትን ከራሳቸው ከ«ጻድቃን» ወይም በሌላ መንገድ ለመዳን የሚሞክሩ በአዳኙ በኢየሱስ ያምናሉን?

አያምኑም፤ በእርሱ ትምክህት ያላቸው ቢመስሉም፣ ነገር ግን በተግባራቸው ግን አንዱን አዳኙን ኢየሱስን ይክዱታል፣ (1) አንድም ኢየሱስ ሙሉ አዳኝ አይደለም፣ ወይም ይሕን አዳኝ በእውነተኛ እምነት የሚቀበሉት፣ ለድነት የሚያስፈልጋቸውን በሙሉ በእርሱ ያገኛል፡(2)

(1)ቆሮ 1÷12-13፤ 30-31፤ ገላ 5÷4፡፡(2) ኢሳ 9÷7፤ ማቴ 23÷28፤ ዩሐ 1÷16፤ ቆላ 1÷19-20፤ 20÷10፤ 1ዩሐ 1÷7፡፡

ሹመቶቹ

12ኛው ሰንበት

31. አዳኛችን ለምን «ክርስቶስ» ወይም የተቀባ ተባለ?

ነቢያችንና መምህራችን ሆኖ በእግዚአብሔር አብ ስለተሾመና በመንፈስ ቅዱስ ስለተቀባ፤(1) ስለመዳናችን ተሰውሮ የነበረውንም የእግዚአብሔርን ምክርናዓላማ ስለገለጠልን፤ (2) እና (3) እያንዳንዱንመሥዋዕት አድርጎ ራሱን በመሰዋት ስለዋጀን እሱ ብቻ ሊቀ ካህናታችን ነው፤ (4) እና (5) ስለእኛም ከአብ ጋር ሲያማድ ዘወትር ይኖራል፡፡ (6) የዘላለም ንጉሣችን በመሆኑ ደግሞ በቃሉና በመንፈሱ ያስተዳድረናል፤ ከጠላቶቻችን ሁሉ ይከላከልልናል፣ ባከናወነልን ድነት እንድንኖር ይጠብቀናል፡፡ (7 እና 8)

(1)መዝ 45÷7 (ዕብ 1÷9)፤ ኢሳ 61÷1 (ሉቃስ 3÷3÷21-22፤ 4÷18፡፡ (2) ዘዳ 18÷15 (ሐሥ 3÷22)፡፡ (3) ዩሐ 1ጳ 18፤ 15÷15፡፡ (4) መዝ 110÷4 (ዕብ 7÷17፣ 21)፡፡ (5) ዕብ 9÷12፤ 10÷11-14፡፡ (6) ሮሜ 5÷9-10፤ 8÷34፤ ዕብ 9÷24፤ 1ዩሐ 2÷1፡፡ (7) ዘካ 9÷9 (ማቴ 21÷5)፤ ሉቃስ 1÷33፡፡ (8) መዝ 2÷6፤ ኢሳ 61÷1-2፤ ማቴ 28÷18-20፤ ዩሐ10÷28፤ 1ጴጥ 2÷24፤ ራዕይ 12÷10-11፤ 19÷16፡፡

32. አንተ ለምን «ክርስቲያን» ተባልክ?

በእምነት የክርስቶስ አባል ስሆን (1) በእርሱም መቀባት ተካፋይ በመሆኔ ነው፡፡ (2) ስለሆንኩም ስለ እርሱ እናገር ዘንድ (3)፣ ሕያው መሥዋዕጥ አድርጌ ራሱን በምስጋና ለእርሱ አቀርብ

ዘንድ፣ (4) በዚህ ህይወት በኃጢያትና ከሰይጣን ጋር በንጹሕ ኅሊና እቃጋ ዘንድ፣ (5) ከዚህም በኃላ በሚመጣው ህይወት በፍጥረታት ሁሉ ላይ ከእርሱ ጋር ስለምነግስ ነው። (6)
(1)ሐሥ 11÷26፤ 1ቆሮ 12÷12-27፤ 1ዩሐ 2÷20፣ 27። (2) ኢዩ 2÷28 (ሐሥ 2÷17፤ 1ዩሐ 2÷27።(3) ማር 8÷38፤ 10÷32፤ ሮሜ 10÷9-10፤ ዕብ 13÷15።(4) ሮሜ 12÷1፤ 1ጴጥ 2÷5፣ 9፤ ራእይ 1÷6፤ 5÷8፣ 10።(5) ገላ 5÷16-17፤ ኤፌ 6÷11፤ 1ጢሞ 1÷18-19።(6) ማቴ 25÷34፤ ኤፌ 6÷12፤ 2ጢሞ 2÷12፤ ራእይ 3÷21።

መለኮትነት

13ኛው ሰንበት

33. እኛ እራሳችን የእግዚአብሔር ልጆች ስንባል፣ እርሱ ግን «የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ» ለምን ተባለ?

ክርስቶስ ብቻ ነው የእግዚአብሔር ዘላለማዊና የባሕርዩ ልጅ ሆነው(1)፣ እኛ ግን የእግዚአብሔር ልጆች ሆነው በጸጋው፣ በክርስቶስ ምክንያትና በእግዚአብሔር አዋጅ ነው።(2)
(1)ዩሐ 1÷1-3፣ 14፣ 18፤ 3÷16፤ ሮሜ 8÷32፤ ዕብ 1፤ 1ዩሐ 4÷9።(2) ዩሐ 1÷12፤ ሮሜ 8÷14-17፤ ገላ 4÷6፤ ኤፌ 1÷5-6፤ 1ዩሐ 3÷1።
34. «ጌታችን» ለምን ትለዋለህ?
ምክንያቱም በብርና በወርቅ ሳይሆን፣ በከበረ ደሙ(1) ነፍሳችንንም ሥጋችንንም ከኃጢአትና ከሰይጣን ኃይል ገዝቶና ዋጅቶ ለራሱ ስላደረገ ነው። (2 እና 3)
(1)ጰዩጥ 1÷188-19።(2) ሐሥ 2÷36፤ 1ቆሮ 6÷20፤ 7÷23፤ 1ጢሞ 2÷5÷6፤ ቲቶ 2÷14፤ 1ጴጥ 2÷9። (3) ቆላ 1÷13-14፤ ዕብ 2÷14-15።

ሥጋ መሆኑ

14ኛው ሰንበት

35. «በመንፈስ ቅዱስ በተጸነሰ፣ ከድንግል ማርያም በተወለደ» ማለት ምን ማለት ነው?

ዘላለማዊው የእግዚአብሔር ልጅ አሁንም ውነተኛና ዘላለማዊ አምላክ የሆነው(1) የሰውን ባህሪይ የራሱ አድርጎ ወሰደ። ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከደሟ ደምን ወስዶ ሰው ሆነ(2)፣ ይሕንም ያደረገው በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ሲሆን (3) ሥጋ በመሆኑም እውነተኛ በሁሉ ነገር ወንድሞቹን መስሏል።(5 እና 6)

(1)ዩሐ 1÷4፤ 10÷30-36፤ ሮሜ 1÷3-4፤ 9÷5 ቆላ 1÷15-17፤ 1ዩሐ 5÷20። (2) ማቴ 1÷18-23፤ ዩሐ 114፣ ገላ 4÷4፤ ዕብ 2÷14።(3) ማቴ 1÷1፤ ሉቃስ 1÷32፤ ሮሜ 1÷3፡ (5) ፊል 2÷7፤ ዕብ 2÷17።(6) ዕብ 4÷15፤ 7÷26-27

36. ከክርስቶስ በቅድስና መጸነስና መወለድ ምን ጥምቅ ታገኛለህ?

እርሱ የኛ አማኟችን ስለሆነ፣ (10 ከበደል ነጻ የሆነው እርሱ በቅዱስነቱ፣ ሲጸነስ ጀምሮ ያለብኝን ኃጢያት በእግዚአብሔር ፊት ይሸፍንልኛል።(2)

(1)1ጢሞ 2÷5-6፤ ዕብ 2÷16-17፤ 9÷13-15።(2) ሮሜ 8÷3-4፤ 2ቆሮ 5÷21፤ ገላ 4÷4-5፤ 1ጴጥ 1÷18-19።

15ኛው ሰንበት

37. «መከራን ተቀበለ» የሚለውን አነጋገር እንዴት ትረዳዋለህ?

በምድር በኖረባቸው ዓመታት በሙሉ፣ በተለይም ወደ መጨረሻው ገደማ በሥጋውና በነፍሱ በኃጢአት ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ቁጣ ተሸከመ፤ ይሕም ኃጢአት የሰው ልጅ ኃጢአት በሙሉ ነው።(1) በዚህም መከራው ስጋችንንና ነፍሳችን ከዘላለም ሕይወት ሊያገኝልን ሲል ነው።(4)

(1)ኢሳ 53፤ 1ጢሞ 2÷6፤ 1ጴጥ 2÷2-4፣ 3÷18።(2) መዝ 22÷14-16፤ ማቴ 26÷38፤ ሮሜ 3÷25-26፤ 5÷6፤ 1ቆሮ 5÷7፤ ኤፌ 5÷2፤ ዕብ 9÷12፣ 1ጴጥ 1÷18-19።(4) ዩሐ 3÷16፤ ሮሜ 3÷24፤ 2ቆሮ 5÷21፤ ዕብ 9÷11።

38. «በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን መከራን ለምን ተቀበለ?»

በጲላጦስ ዳኝነት ማለት ነው። እርሱ ምንም በደል ሳይኖርበት በምድራዊው ፈራጅ ይፈረድበት ዘንድ (1)፣ በዚህም

ከተጋለጥንበትና እጅግ ከባድ ከሆነው እግዚአብሔር ፍርድ እኛን ለማዳ ሲል ነው። (2)

(1)ሉቃስ 23÷13-24፤ ዩሐ 19÷4፤ 12-16፤ ሐሥ 4÷27-28።

(2) መዝ 69÷4፤ ኢሳ 53÷4-5፤ ማቴ 27÷24 2ቆሮ 5÷21፤ ገላ 3÷13።

39. በሌላ አሟሟት ሳይሖን ነገር ግን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በመሞቱ የተለየ ጥቅም አለውን?

አዎ፣ የመስቀል ሞት በእግዚአብሔር የተረገመ ስለሆነ፣ በዚህ አሟሟቱ በላይ የነበረውን ርግማን በራሱ እንደወሰደልኝ ርግጠኛ እንድሆን አድርጎኛል። (1 እና 2)

(1)ገላ 3÷13-14።(2) ዘዳ 21÷22-23፤ ፊል 2÷8

16ኛው ሰንበት

40. ክርስቶስ መሞት ለምን አስፈለገው?

ለነጢአት ዋጋ በእግዚአብሔር ልጅ ሞት ብቻ እንጂ በሌላ በማንም ሊከፈል የማይቻ መሆኑን የእግዚአብሔር ፍርድና እውነት ስላስገደዱ ነው። (1 እና 2)

(1)ዘፍ 2÷17።(2) ሮሜ 6÷23፤ ፊል 2÷8፤ ዕብ 2÷9፤ 14-15።

41. ለምን«ተቀበረ»?

በርግጥ መሞቱን ለማሳየት። (1)

(1)ኢሳ 53÷9፤ ማቴ 27÷59-60፤ ዩሐ 19÷38-42፤ ሐሥ 13÷29፤ 1ቆሮ 15÷3-4።

42. ክርስቶስ ሞቶልን ሳለ፣ እኛ ታዲያ ለምን እንሞታለን?

የእኛ ሞት ለነጢያት ዋጋ ለመክፈል አይደለም፤ ነገር ግን ለነጢአት እንድንሞትና ወደ ዘላለም ሕይወት እንድሸጋገርበት ነው እንጂ።(1)

(1)ዩሐ 5÷24፤ ሮሜ 7÷24-25፤ ፊ 1÷21-23፤ 1ተሴ 5÷9-10።

43. ከክርስቶስ በመስቀል ላይ መሥዋዕት ሆኖ በመሞቱ ምን ተጨማሪ ጥቅም እናገኛለን?

የእርሱ ኀይል፤ አሮጌው ሰው ከእርሱ ጋር ተሰቅሏል፣ ተሰይፏል፣ ተቀብሯል፤ (1) ስለዚህ የስጋ መጥፎ ፍላጎቶች በእኛ

ላይ ሊሰለጥኑብን አይችሉም።(2) ነገር ግን ራሳችንን ለእርሱ ሕያው መሥዋዕት አድርገን ማቅረብ አለብን።(3)
(1)ሮሜ 6÷5-11፤ ቆላ 2÷11-12።(2) ሮሜ 6÷12-14።(3) ሮሜ 12÷1፤ 2ቆሮ 5÷15፤ ኤፌ 5÷1-2።

44. «ወደ ሲኦል ወረደ» የሚለው ለምን ተጨመረ?

በታላቅ ፈተና ውስጥ የወደቅሁ ጊዜ ክርስቶስ ጌታ በመስቀሉ ላይኛ ከመስቀሉ በፊት በቃላት ሊገለጥ በሚቻለው በነፍሱ በተቀበለው ስቃዩ፣ መከራውና ድንጋጤው ከሲኦል መከራና ስቃይ እንዳዳነኝ ርግጠኛ እሆን ዘንድ።(1)
(1)መዝ 18÷5፤ 116÷3፤ ኢሳ 53፤ ማቴ 26÷36-46፤ 27÷46፤ ዕብ 5÷7-10።

ትንሣኤው

17ኛው ሰንበት

45. ከክርስቶስ ትንሣኤ ምን ጥቅም እናገኛለን?

በመጀመሪያ፣ በትንሣኤው ሞትን አሸንፏል። በዚህም ትንሣኤ በሞቱ ያገኘልንን ጽድቅ ለኛለማስተላለፍ ችሏል። (1) ሁለተኛ፣በእርሱ ኀይል እኛም ደግሞ ለአዲስ ሂወት ተነስተናል። (2) ሶስተኛ፣የክርስቶስ ትንሳኤ ለእኛ ለተባረከው ትንሳኤያችን ርግጠኛ የሆነ ዋስትናችን ነው። (3)

(1) ሮሜ 4÷25፤1ቆሮ 15÷15-20፣54-55፤1ጴጥ 1÷3-5፣ 21። (2) ሮሜ 6÷5-11፤ኤፌ 2÷4-6፤ቆላ 3÷1-4። (3) ሮሜ 8÷11፤1ቆሮ 15÷12-23፤ፊል 3÷20-21።

ዕርገቱ

18ኛው ሰንበት

46እርሱ ወደ መንግሰተ ሰማይ አርጓል ስትል ምን እያመንክ ነው?

ክርስቶስ በደቀመዛሙርትነት ዓይን ፊት ከምድር ወደ ሰማይ ሲወስድ (10 ዳግምም ዳግም እስኪመለስ ድረስ በዚያ መሆኑ ለእኛ ጥቅም ነው።(2) በህያውያንና በሙታን ላይም ይፈርዳል(3)

(1) ማር 16፡19 ሉቃ 24፡50,51,ሐሥ 1፡9-11(2) ሮሜ 8፡ 34,ዕብ 4፡14,7፡23-25፣9፡24(3) ማቴ 24፡30,ሐሥ 1፡11

(2) 47. ክርስቶስ ቃል እንደገባልን እስከ ዓለም ፍፃሜ አብሮን አይሆንም ማለት ነው? (1)

ክርስቶስ እውነተኛ ሰው እና እውነተኛ እግዚአብሄር ነው ምድር ብዙ አልቆየም (2) ነገር ግን መለኮታዊነቱ ፣ ግርማው፣ጸጋው ፣መንፈሱ በፍፁም እኛን አይለየንም።(3)

(1) ማቴ 28፡20 (2) ማቴ 26፡11 ዮሐ 16፡28፣17፡11 ሐሥ 3፡19-21 ዕብ 8፡4 (3) ማቴ 28፡18-20 ዮሐ 14፡16-19፡13

48. ነገር ግን በክርስቶስ ያሉት ሁለት ተፈጥሮዎች ሊለያዩ አይችሉ?ም ማለትም ከመለኮት ውስጥ ሰዋዊ ተፈጥሮ እንዴት አይደለም?

በጭራሽ መለኮታዊነቱ የትም ከመሆን አይገድብም። (1) ስለዚህም ሰዋዊ ተፈጥሮ ባሻገር መለኮታዊነቱን ይከተላላ በሰውነቱ ውስጥም መለኮታዊነት አንድ ሆኗል። (2)

(1) ኤር 23፡23-24 ሐሥ 7፡48-49 (20 ዮሐ 1፡14፣3፡13 ቆላ 2፡9

49. የክርስቶስ ዕድገት ለእኛ የሚመጣው ጥቅም ምንድን ነው?

አንደኛው እርሱ በሰማይ በአብ ፊት ጠበቃችን ነው። (1)

ሁለተኛው አካላችን በሰማይ ነው። የእኛ ራስ እርሱ ባለበት ሁለታችንም ይወስደናል።(2) ሶስተኛው እርሱ መንፈሱ እንደ መያዣ ሰጥቶናል (3) በላይ ያለውን ነገር ክርስቶስም ያለበትን ሥፍራ በእግዚአብሄር ቀኝ የተቀመጠበትን ዳግም በምድር የሌሉትን ነገሮች እናውቅ ዘንድ (4)

(1) ሮሜ 8፡34፣ 1ዮሀ 2፡1 (2) ዮሐ 14፡2፣17፡24፣ኤፌ 2፡4-6 (3) ዮሐ 14፣16 ሐሥ 2፡33,2ቆሮ 1፡21,22፡ 5-5 (40 3፡1-4

19ኛው ሰንበት

50. እርሱ እግዚአብሄር ቀኝስ ለመን ተቀመጠ?

ክርስቶስ ወደ ሰማይ ሄዷል።(1) በዚያም የቤ/ክ ራስ መሆኑን ሁሉን በሚገዛ አብ በኩል ይገልጥ ዘንድ ነው።(2)

(1) ኤፌ 1፡20-23, ቆላ 1፡18 (2) ማቴ 28፡18 , ዮሐ 5፡22-23

51. ራስ የሆነን የክርስቶስ ክብር እንዴት ይጠቅመን ዘንድ አለ?

በቅድሚያ በመንፈስ ቅስ በኩል የእርሱ ለሆኑት ሰማያዊ ስጦታዎች ይፈሳሉ። (1) በተከታታይመ እርሱ በኃይሉ ከጠላቶቻችን ሁሉ ይጠብቀናል። ይከላከልልናልም ።(2) (1) የሐዋ ሥራ 2፡33 , ኤፌ 4፡7-12 (2) መ.ዳዊት 2፡9 110፡1,2,ዮሐ 10፡27-30 ራዕ 19፡11-16

52. የክርስቶስ በህያዊያንና በሙታን ላይ ሊፈርድ መመለሱላንት ምን ይሰጥሀል?

ካለብኝ ሀዘን እና በደል ሁሉ ራሴን ቀና አድርጌ አስቀድሞ ራሱን ለእኔ ፍርድ አሳልፎ በሰጠ እንዲሁም መርገጫን ሁሉ ከእኔ የሚያስወፈግድ ፍርድን እናሳውቀዋለን ።(1) እርሱ የእኔና የእርሱን ጠላቶች ግን እኔንና የርሱን የሆኑትን ሁሉ ክብር እና ደስታ ወደ ሞላበት መንግስተ ሰማይ ይወስደናል።(2) (1) ሉቃ 21፡28 ሮሜ 8፡25 ፊሊ 3፡20፣21 ቶቶ 2፡13,14 (20 ማቴ 25፡31-46፣ተስ 4፡16፣17 2ተስ 4፡16፣17 2 ተስ 1።6-10

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ እና መቀደሳችን

20ኛው ሰንበት

53. መንፈስ ቅዱስ በተመለከተ ያለህ እምነት ምንድንነው?

በቅድሚያ እርሱ ከአብና ከወልድ ጋር እውነተኛ እና ዘላለማዊ አምላክ ነው። (1)

በተለይም ደግሞም እውነተኛ እምነትን ይሰጠኝ ዘንድ (2) ደግሞ የክርስቶስ የሆነውን ሁሉ ተካፋይ መሆን እንድችልና(3) ሁሌም አብሮኝ(4) ሊኖር ተሰጥቶኛል።(5)

(1)ዘፍ1፡1፣ ማቴ28፡19፣ የሐዋ ሥራ 5፡3-4፣ 1ቆሮ 3፡16 (2) 1ቆሮ 6፡19 2ቆሮ 1፡21፣22 ገላ 4፡6 ኤፌ 1፡13 (3)ገላ 3፡14፣ 1ጴጥ 1፡2 (4)ዩሐ 15፡26-የሐዋ ሥራ 9፡31 (5)ዩሐ 14፡16,17፣1ጴጥ 4፡14

21ኛው ሰንበት

54. ቅድስት ካቶሊክ የክርስቲያን ቤ/ክ በተመለከተ ያለህ አስተሳሰብ ምንድን ነው?

በእግ/ር ልጅ አምናለሁ (1) ከሰው ዘር ሁሉ ውስጥ (2) ከዓለም መጀመሪያ እስከ ፍፃሜ(3) የሰበሰባቸውንና ለራሱ የጠበቃችን (4) በእርሱ መንፈስና በቃሉ (5) ለዘላለም ህይወት በተመረጠች ቤ/ክ (7) እና እኔም ያንን በማመን(8) በመጨረሻም ለዚህ ህያው አባልነት፡፡ (9)

(1)ዮሐ 10፡11 የሐዋ ስራ 20፡28 ኤፌ 4፡11-13 ቆላ 1፡18 (2) ዘፍ 26፡4 ራዕ 5፡9 (3) ኢሳ 59፡21 1ቆሮ 11፡26 (4) መዝ 129፡1-5 ማቴ 16 ዮሐ 10፡28-30 (5) ሮሜ 1፡16 10፡17-17 ኤፌ 5፡26 (6) የሐዋ ስራ 4፡42-47 ኤፌ 4፡1-6 (7) ሮሜ 8፡ 29 ኤፌ 1፡13-14 (8) 1ዮሐ 3፡6 ዮሐ 10፡27-28 1ቆሮ 1፡4-9 1ጴጥ 1-3-5

55. ስለ ቁዱሳን አንድነት ያለን ግንዛቤ ምንድ ነው?

በቅድሚያ በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ ከእርሱ ጋር ህብረት አለው እንዲሁም የእርሱን ባለጠግነት እና ስጦታ ይከፍላል (1) በከታይም ሁሉም የእርሱን ፀጋ ያለ ዋጋ በለጋስነት ሊሰጥ ይገባዋል፡፡ ይህም ለሌሎች ሙላት ጥቅም ይሆን ዘንድ ነው፡፡

(1) ሮሜ 8፡32 1ቆሮ 6፡17፣ 12፡4-17 12፡13፣ 1ዮሐ 1፡3 (2) ሮሜ 12፡4-8፣ 1ቆሮ 12፡20-27፣ 13፡1-7 ፊል 2፡4-8

56. የሐጢያት ይቅርታን በተመለከተ ያለህ እምነት ምንድን ነው?

እግዚአብሔር በክርስቶስ ስራ የረካ በመሆኑ የእኔን ሐጢያተኛ ተፈጥሮዬን በዘመኔ ሁሉ እንደሚታገለው ነገር ግን በክርስቶስ ፅድቅ ፀጋው አድኖኛል ያም መቼም ወደ ኩነኔ አልመለስም፡፡

(1) መዝ 10፡3፣4፣10፣12 ሚክ 7፡18-19 2ቆሮ 5፡18-21 1ዮሐ 1፡7፡2-2 (2) ሮሜ 7፡21-25 (3) ዮሐ 3፡17-18 5፡ 24 ሮሜ 1፣2

22ኛው ሰንበት

57. አፅናኙ በትንሳኤ አካል ምንን ሊሰጥህ ይችላል?

ከዚህ ህይወት በኃላ የምትነሳው ነፍሴ ብቻ አይደለችም። (1) ይልቁንም ስጋም በክርስቶስ ኃይል ይነሳል ከነፍሴም ጋር ይዋሃዳል የክርስቶስን ክብር ስጋ እስከሚመለስ ድረስ። (2) (1) ሉቃ 16፡22፣23-24 ፊል 1፡21-23 (2) ኢዮ 19፡25-26 1ቆሮ 15፡20፣42-46-54 ፊሊ.. 3፡21 1ዮሐ 3፡2

58. ዘላለማዊ ህይወት ከሚለው ቃል ምን አዕናኝ ነገር አገኘህ?

አሁን በልቤ እየጀመረ ያለና የሚሰማኝን ዘላለማዊ ደስታ(1) ከዚህ ህይወት በኃላም ፍፁሙን ባርኮት ማለትም ዓይን ያላየውን ጆሮ ያላሰማውን በሰው ልብ ያልታሰበውን ባርኮት ይህም እግዚአብሔርን ለዘለአለም የማመሰግንበትን አገኛለሁ። (2)

(1)ዩሐ 17፡3፤ ሮሜ 14፡17፣ 2ቆሮ 5፡2-3፣ (2)ዩሐ 17-24፣ 1ቆሮ 2፡9

ጽድቃችን

23ኛው ሰንበት

59. አሁን ይህን ሁሉ ማመንህ ላንተ ያለው ፋይዳ ምንድን ነው?

እኔ በክርስቶስ በእግ/ር ፊት ፅድቅ እና ለዘላለም ህይወት ወራሽነት ተመርጫለሁ

ዕን 2፡4፣ ዩሐ 3፡36፣ ሮሜ 1፣ 17 5፡1-2

60. በእግ/ር ፊት ፅድቅ መሆን እንዴት ቻልክ?

በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ብቻ! ህሊናዬ በእግ/ር ፊት ህጉን አንዲንም አልጠበቅክም እያለ ቢሰኝም ዕስካሁን የክፉ ሥራ ዝንባሌ ቢኖረኝም እግ/ር ግን ያለ እኔ መልካም ድርጊት በፀጋው ብቻ እኔን በፍፁም ደስታ ፅድቅ እና ክርስቶስ ቅዱስ አደረገን እርሱ እነዚህን ሁሉ አረጋገጠልኝ። አንዳችም በደል እንደሌለኝ መታዘዝንም ልፈፅም እንዳለመቻሌ ክርስቶስ ግን ራሱን ለእኔ አቀረበልኝ ይሕ ሁሉ፤ ይህንን ስጦታ ከልቤ በማመን ይሆናል።

(1)ሮሜ 3፡21-28 ገላ 2፡16 ኤፌ 2፡8-9 ፊል 3፡8-11 (2) ሮሜ 3፡9-10 (3) ሮሜ 7፡23 (4)ዘዳ 9፡6 ሕዝ 36፡22 ቶቶ 3፡4-5 (5)ሮሜ 3፡24 ኤፌ 2፡8 (6) ሮሜ 4፡3-5 2ቆሮ 5፡21 (8)ዩሐ 3፡18 የሐዋ ሥራ 16፡30-31 ሮሜ 3፡22

61. በእምነት ብቻ ፀደቅ ስትል ምን ማለት ነው?

እኔ ባለኝ ሁኔታ በእግ/ር ፊት በዚህ የሚያበቃ ነገር ኖሮኝ ሳይሆን በክርስቶስ በእግ/ር ፊት ያለው ፅድቅ ቅድስናን አርኪ ሥራ ነው። ለዚህ ያበቃኝ በዚህ ነው ይህንን ፅድቅ በእምነት ብቻ ልቀበለው የቻልኩት።

(1)ቆሮ 1፡30-31፣ 2፡2 (2)ሮሜ 10፡10፣ 1ዩሐ 5፡10-12

24ኛው ሰንበት

62. የእኛ መልካም ሥራዎች ግን ለምንድን ነው?

በእግ/ር ፊት ፅድቅ የማይሆኑት ወይንም ትንሽ ድርሻ እንኳን የማይኖራቸው?

ምክንያቱም በእግ/ር ፍርድ ፊት የሚቆም ፅድቅ የግድ እጅግ ፍፁም የሆነ እና ከእግ/ር ህግ ጋር የተሟላ ስምምነት ሊኖረው ይገባል። በዛው ልክ የኛ እጅግ ጥሩ የምንለው ሥራችን እንኳን ብቁ ያልሆኑና በሐጢያት የረከሰ ነው።

(1)ዘዳ 27፡26፣ ገላ 3፡10 (2)ኢሳ 64፡6

63. መልካም ሥራዎችን ምንም አያተርፍም ማለት ነው?

እንዲሁም እግ/ር በዚህ ህይወት ወይንም በሚመጣው ሊሸልም ቃል የገባውስ ሽልማቱ ይህን ማትረፍ ሳይሉን ስጦታ ወይንም ፀጋ ነው።

(1)ማቴ 5፡12 ዕብ 11፡6 (2)ሉቃ 17፡10 2ጢሞ 4፡7-8

64. ይህ አስተምሮ ግን ሰዎችን ግድየለሽና ሰነፍ አያደርጋቸውም?

በጭራሽ ሊሆን የማይችለው ነገር እነዚህ በእምነት ከክርስቶስ ፍሬን አያመጡም።(1)

(1)ማቴ 7፡18 ሉቃ 6፡43-45 ዩሐ 15፡5

ቃሉ እና የፀጋ መሳሪያዎች

25ኛው ሰንበት

65. እምነት ብቻውን ክርስቶስ እና የእርሱ የሆነውን ካካፈለን ይህ እምነት ከየት ነው ሊመጣ የሚችለው?

ከመንፈስ ቅዱስ ያም በሚሰበከው ወንጌል በልባችን የሚሰራ ሲሆን ሊያፀናንም ይችላል። ይህም በፀጋ መሳሪያው በኩል ነው

(1)ዩሐ 3፡5፣ 1 ቆሮ 2፡10-14 ኤፌ 2፡8 ፊሊ 1፡29 (2)ሮሜ 10፡17፣ 1ጴጥ 1፡23-25 (3) ማቴ 28፡19-20 1ቆሮ 10፡16

66. የፀጋ መሳሪያዎች ምን ምንድናቸው?

የጸጋ መሳሪያዎች ቅዱስ የሚታይ ምልክት ያለውን የተረጋገጠ ነው። የተመሰረቱም በእግ/ር ሲሆን እርሱም የጥቅሙን ዘንድ በወንጌል ውስጥ ቃል ገብቶ በሙላት ታውጇል፡ ፡ ይህም ቃል ኪዳን እግ/ር በፀጋው የሐጢያት ይቅርታንና የዘላለም ህይወትን ዋስትና ሰጥቷል ምክንያቱም የክርስቶስ መስዕዋትነት በመስቀል ላይ ተፈርሟል።

(1)ዘፍ 17፡11፣ ዘዳ 30፡6 ሮሜ 4፡11 (2)ማቴ 26፡27-28 የሐዋ ሥራ 2፡38 ዕብ 10፡10

67. ሁለቱም ቃሉና የፀጋው መሳሪያ በእምነታችን ላይ እንድናተኩር ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈረመውን የደህንነታችንን መስዕዋት የሚያሳዩ ናቸውን?

አዎ። በእርግጥ መንፈስ ቅዱስ በወንጌላት ላይ እንደሚያስተምረን እና እንደሚረጋግጥልን ክርስቶስ ባደረገው መስዕዋት እና በፀጋው መሳሪያው በኩል ደህንነታችን ሙላት ያገኛል።(1) (1)ሮሜ 6፡31 1ቆሮ 11፡26 ገላ 3፡27

68. በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ስንት የፀጋ መሳሪያዎችን አቋቁሟል?

ሁለት ቅዱስ ጥምቀት እና ቅዱስ ቁርባን።(1)

(1)ማቴ 28፡19-20, 1ቆሮ 11:23-26

ቅዱሽ ፅምቀጽ

26ኛ ሳምንት

69. ክርስቶስ በመስቀል ያደረገውን መስዕዋት ይጠቅምህ ዘንድ በቅዱስ ትምቀት እንዴት ልታረጋግጥ ትችላለህ?

በዚህ መንገድ ክርስቶስ ውጫዊውን መታጠብ ሲያቋቁም እና በዚያም የገባው ቃልኪዳን እርግጠኛ የሆነ የሰውነት እድፍ መንፃት ይኖራል ስለሆነም የጌታ ደም እና መንፈሱ ከነፍሳችን ላይ ያለውን ሙሉ ሐጢያት ያነፃል።

(1)ማቴ 28፡19 (2)ማቴ 3፡11 ማር 16፡16 ዩሐ 1፡33 የሐዋ ሥራ 2፡38 ሮሜ 6፡3-4 1ጴጥ 3፡21

70. በክርስቶስ ደም እና መንፈስ መታጠብ ማለት ምን ማለት ነው?

በክርስቶስ ደም መታጠብ ማት በፀጋው በኩል ከእግ/ር የሐጢያት ይቅርታን መቀበል ማለት ነው። ምክንያቱም የክርስቶስ ደም መስዕዋታችን ሆኖ በመስቀል ላይ ፈሶልና። በመንፈስ መታጠብ ማለት በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ማለት ነው።

እንዲሁም የክርስቶስ አካ ለመሆን መቀደስ ማለት ነው። ስለሆነም ይበልጥ ለሐጢያት ሙት እየሆንን የምንመጣ ሲሆን የተቀደሰና ከወቀሳ የዳነ ሂወት ለማግኘት በእርሱ መመራት ማለት ነው።

(1)ሕዝ 36፡25 ዘካ 13፡1 ኤፌ 1፡7 ዕብ 12፡24 1ጴጥ 1፡2 ራዕ 1፡5 7፡14 (2)ዩሐ 3፡5-8 ሮሜ 6፡4 1ቆሮ 6፡11 ቆላ 2፡11-2

71. ክርስቶስ በኪዳኑ በዳመና መንፈሱ እንደሚፀናን ቃል የገባ ሲሆን በውሃ ጥምቀት እርግጠኛ መንፃት እናገኛለን?

እርሱ ጥምቀትን ባቋቋመ ጊዜ እንዲህ አለ።(1)

(1)ማቴ 28፡19፣ ማርቆ 16፡16፣ ጥቅሶች ይፅፋሉ

27ኛው ሳምንት

72. ውጫዊው መታጠብ በራሱ ከሐጢያት መንፃትን ያደርጋልን?

አያደርግም የኢየሱስ ክርስቶስ ደምና መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው ከሐጢያት የሚያነፃን።(1)

(1)ማቴ 3፡11 1ጴጥ 3፡21 1ዩሐ 1፡7

73. መንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን የዳግም ልደት መታጠብ እና ሐጢያት የሚያርቅ መታጠብ ሲል ለምን ያስረዳናል?

ውሃ የሰውነትን እድፍ እንደሚያስወግድ ሁሉ የክርስቶስ ደም እና መንፈስ ሀጢያታችንን ያስወግደዋል። ነገር ግን ከዚህ በሚበልጥ ሊያረጋግጥልን የሚፈልገው ነገር በመለኮታዊ መተማመኛ እና ማህተም ከሐጢያታችን እውነተኛ መንፈሳዊ መንገዶች ልክ ሰውነታችን በውሃ የሚያገኘውን መንፃት እናገኛለን።(2)

(1)ቆሮ 6፡11 ራዕ 1፡5 7፡14 (2)ማር 16፡16 የሐዋ ሥራ 2፡38 ሮሜ 6፡3-4 ገላ 3፡27

74. ሕፃናትስ ሊጠመቁ ይገባቸዋልን?

አዎ። ሕፃናትም ሆነ አዋቂዎች እግ/ር ቃል ኪዳን ተካፋዮችና ማህበር ናቸው። በክርስቶስ ደም በኩል ከሐጢያት

ተዋጅተናል እንዲሁም እምነትን በሚፈጥልን በመንፈስ ቅዱስ በኩል ከአዋቂዎች ያለው ቃል ተገብቶላቸዋል
(1)ዘፍ 17፡7 ማቴ 19፡14 (2) መዝ 22፡10 ኢሳ 44፡1-3 የሐዋ ሥራ2፡38-39 (30የሐዋ ሥራ 10፡47 1ቆሮ 7-14 (4)ዘፍ 17፡9-14 (5)ቆላ 2፡11-13

የጌታ እራት
28ኛው ሰንበት

75. የጌታ እራት ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ የፈጸመውን መስዕዋት እና ስጦታዎችን እንዴትስ ሊያካፍለን ይችላል በዚህ መንገድ?

ክርስቶስ እነተን አማኞችን ሁሉ ህብስቱን እንድንበላና ፅዋውን እንድንጠጣ ያንን መታጠቢያው እንድናደርግ አዟልና በዚህ ትዕዛዝ ውስጥ የሚከተሉትን ተስፋዎች ሰጥቷል። በቅድሚያ ወይኖች በትክክል ህብስቱን ላዩ ስለ እኔ የተቆረሰ ሥጋውን በደሙ የተከለናወነ ነው።(1)
(1)ማቴ 26፡26-28 ማር 14፡22-24 ሊቃ 22፡19-20 1ቆሮ 11፡23-25

76. የተሰዋውን ስጋ መብላት የፈሰሰ ደሙን መጠጣት ማለት ምን ማለት ነው?

በቅድሚያ የክርስቶስን ስቃይና ሞት በሚያምን ልብመቀበል እናም የሐጢያት ይቅርታንና ዘላለማዊ ህይወት መቀበል በተከታይም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ይበልጥ ቅዱስ ሥጋው ጋር ህብረት ለማድረግ እርሱም በእኛ እና በእርሱ የምንኖረው ክርስቶስ ነው። ስለዚህ ክርስቶስ በሰማይ እና በምድር ነን ግን ሥጋችን የእርሱ ስጋ አጥንታችን የእርሱ አጥንት እናም እኛ ለዘላለም የምኖር በአንድ መንፈስ የምንገዛ እንደ ሰውነት አካሎቻችን በአንድ ህይወት ያለን ነን።(5)
(1)ዩሐ 6፡35-40 50-54 (2)ዩሐ 6፡55-56 1 ቆሮ 11፡226 ቆላ 3፡1 (3) የሐዋ ሥራ 1፡9-11 3፡21 1ቆሮ 11፡26 ቆላ 3፡11 (4) 1ቆሮ 6፡15-17 ኤፌ 5፡29-30 1ዩሐ 4፡13 (5) የሐ 6፡56-58፣ 1-6 ኤፌ 4፡15-16 1ዩሐ 3፡24

77. ክርስቶስ የአማኞችን ህይወት ለማደስና ለመመገብ ሥጋና ደሙን በማሰብ ህብስቱን በመብላትና ፅዋውን በመጠጣት ተስፋን የሰጠበት ሥፍራ የት ነው?

የጌታ እራት በተመሰረተበት ቦታ 1ቆሮ 11፡23-26 ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመሰገነ ቆርሶም እንካችሁ ብሎ ይ ስለእናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው ይህም ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።

ይህ ተስፋ በጳውሎስ እንዲሁም ሲል ተደግሟል። 1ቆሮ 10፡16-17 የ ምንባርከው የበረከት ከክርስቶስ ደም ጋር ህብረት ያለው አይደለም? አንድ እንጀራ ስለሆነ እኛ ብዙዎቹ ስንሆን አንድ ሥጋ ነን ሁላችን ያለን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንናና፡ ይፈረድበታል(2) ባለው ቃል ላይ ይገኛል። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ጥምቀትን የዳግም ልደት መታጠብ ሲለውና (3) ኃጢአትን መታጠብ(4) ሲለው ይህ የተስፋ ቃ በድጋሚ ነግሯል፡ : (1) ማቴ 28፡19። ማር 16፡16። (3)ቲቶ 3፡5። (4) ሐሥ 22፡ 16።

29ኛው ሰንበት

78. ታዲያ እንግዲህ ኅብስቱንና ወይኑ ወደ እውነተኛ የክርስቶስ ሥጋና ደም ይለወጣሉን?

አይ። አይለወጡም። ነገር ግን የጥምቀት ውሃ ወደ ክርስቶስ ደም እንደማይለወጡም ሁሉ፣ ጥምቀት ራሱም ከአምላክ የሚሰጥ ምልትና ማረጋገጫ እንጂ(1) ራሱ ኃጢአትን የሚያጥብ እንዳልሆነ ሁሉ፣ እንዲሁም ለጌታ ራት የሚቀርበው ቅዱስ ኅብስትም ምን እንኳ በሃይማኖት የምሥጢር አነጋገር የክርስቶስ ሥጋ(2) ቢባልም፣ ራሱ ወደ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋነት አይለወጥም። (3፣4)

(1)ኤፌ 5÷26 ቲቶ 3÷5 (2)ማቴ 26÷26-29 (3)1ቆሮ 11÷26-28 (4)ዘፍ 17÷10-11 ዘጸ 12÷11 13÷26-27 43 48 1ቆሮ 10÷1-4 16-17 26-28

79. ታዲያ ለምንድነው ክርስቶስ ኅብስቱን ሥጋው፣ ጽዋውን ደግሞ ደሙ ይለዋል እንዲሁም በደሙ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው ለምን አለው?

ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ ኀብስቱና ወይኑ ከክርስቶስ ሥጋና ደም ለምን ኀብረት አላቸው አለ ክርስቶስ እንደዚህለመናገር ትልቅ ምክንያትአለው። ይህም ምክንያት እኛን ለማስተማር ብቻ ሳይሆን፣ ማለትም ኀብስትና ወይን ለሥጋዊ ሕይወታችን መኖር መሣሪያ እንደሆኑ ሁሉ፣ (1) ተሰቀለው ሥጋውንና የፈሰሰ ደሙን ነፍሳችን ለዘላለም እንድትኖር የሚያስፈልጋት እውነተኛ ምግብ ነው፣ ከዚህም በላይ ደግሞ በዚህ በሚታ ምልክት እኛ ከክርስቶስ እውነተኛ ሥጋና ደም በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ተካፋይ ለመሆናችን የሚሰጠን ምልክትና ዋስትና ነው።(2) የመታሰቢያ የሆነውን የሥጋውን ምሳሌ ኀብስቱን በአፋችን እንደምንወስደው ሁሉ. እንዲሁም የክርስቶስን መከራና መታዘዝ የእኛ የግላችን መከራና መታዘዝ አድርገን የምንቀበልበት መሣሪያም ስለሆነ ነው።(3) (1)ዩሐ 6-51-55 (2)1ቆሮ 5÷16-17 10÷26 (3)ሮሜ 6÷5-11

30ኛው ሰንበት

80. በጌታ እራትና በጳጳሱ ቁርባን ምን ልዩነት አለ?

ለዘላለም አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ በቀረበልን በአንድ በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት ምክንያት ሙሉ የኃጢአት ይቅርታን የተቀበልን መሆናችንን የጌታ ራት ይመሰክርልናል፣(1) እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ውስጥ የተተከልን መሆናችንን የጌታ ራት ይመሰክርልናል፣ ክርስቶስ በእውነተኛ ሥጋው አሁን በአብ ቀኝ በሰማይ ቤት ይገኛል፣ በዚያም ሳለ ይመለካል። ነገር ግን የሮማ ካቶሊክ ማስ (ቁርባን) ክርስቶስ በየቀኑ በቀሳውስቱ ለእነርሱ ካልተሰዋላቸው በስተቀር፣ ክርስቶስ መከራ አማካይት ሕያዋኑና ሙታኑ የኃጢአት ይቅርታን አያገኙም ብሉ ያስተምራል። ስለዚህ ማስ (ቁርባን) ተባለው ያን አንድን የኢየሱስ ክርስቶስን የመስቀል መከራ የሚክድ ትምህርት ስለሆነ የተረገመ ጣዖት ነው ማለት ነው። (2፣3፣4)
(1)ማቴ 26÷28 ዩሐ19÷30 ዕብ 7÷12 25÷28 10÷10-12 14 (2)1ቆሮ 6÷17 10÷16-17 (3)ዩሐ 20÷17 ሐሥ 7÷55-56 ዕብ1÷3 8÷1 ሉቃስ24÷52 (4)ዩሐ 4÷21-24 20-17

ሐሥ 7÷25 ፊል 3÷20-21 ቆላ 3÷1 1ተሰ 1÷9-10 ማቴ 4÷10 ዕብ9÷10

81. ወደ ክርስቶስ ገበታ ወይም ወደ ጌታ ራት የሚቀርቡት እነማናቸው?

ስለ ኃጢአታቸው ራሳቸውን የተጸየፉ፣ ነገር ግን እነዚያ የሚጸየፏቸው በይቅርታ እደተወገደላቸው የሚተማመኑ፣ እንዲሁም አሁን ያሏቸው ድካሞቻውበክርስቶስ መከራና ሞት የተሸፈኑላቸው መሆናቸውን የሚያምኑ፣ በየዕለቱም እምታቸውን ሊያጠነክሩ የሚፈልጉ ሁሉ ናቸው። ነገር ግን ንስሐ የማይገቡና ግብዞች ደፍረው ወደ ጌታ ራት ከቀረቡ ለራሳቸው ፍርዱን ይበላሉ፣ ይጠጣሉ።(1)

(1)መዝ 51፡3 103÷1-4 ማቴ 5÷6 የሐ 7÷37-38 1ቆሮ 10÷19-22 11÷26-32

82. በአነጋገራቸውና በሕይወታቸው የማያምንና ፈሪሐ እግዚአብሔር የሌላቸው መሆናቸውን የሚገልጡ ወደ ገበታው ሊቀርቡ ይገባቸዋልን?

በፍጹም። እንደነዚህ ባሉ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ስለሚረክስና ቁጣው በማህበሩ ሁሉ ላይ ስለሚገለጥ፣ ሕይወታቸውን እስኪያስተካክሉ ድረስ እንደዚህ ያት ወደ ገበታው እንዳይቀርቡ ክርስቶስ በሰጣት የመንግስተ ሰማይ መክፈቻ እንደትከለክል የክርስቶስ ቤት ክርስቲያን ጥብቅ ትዕዛዝን ከክርስቶስና ከሐዋርያቱ ተቀብላለች።(1)

(1)መዝ 50÷13-17 ኢሳ 1÷11-17 66÷3 ኤር 7÷21-23፣ ማቴ 7÷6 1ቆሮ11÷17-34 2ተሰ 3÷6 ቲቶ 3÷10-11

ስብከትና ቅጣት

31ኛው ሰንበት

83. የመንግስሥተ ሰማይ መክፈቻ ሥልጣን ምድን ነው የቅዱስ ወንጌል ስብከትና የክርስትና ቅጣት ናቸው?

ለእነዚህ በሁለቱ አማካኝነት የእግዚአብሔር መንግሥጥ ለሚያምኑት ይከፈላቸዋል ለማያምኑት ደግሞ ይዘጋባዋል።(1)

(1)ማቴ 16÷18-19 18÷18 ሉቃ 24÷46-47 ዩሐ 20÷21-23 1ቆሮ 1÷23-24

84. በቅዱስ ወንጌልስብከት አማካይነት የእግዚአብሔር መንግስት የሚመለከተውና የሚዘጋው እንዴት ነው?

በክርስቶስ ትእዛዝ መሠረት ወንጌል ለእያንዳንዳቸው ለምእመናን በግልጥ የታወጅላቸው፣ ይመስከርላቸዋል፣ የወንጌልን የተስፋ ቃል በተቀበሉና ባመኑ ቁጥር ስለ ክርስቶስና ስለ ክርስቶስና ስለ ክርስቶስ የማዳን ተግባር ኃጢአታቸው በሙሉ በእግዚአብሔር ይቅር ይባሉላቸዋል። በአንዛፉም አስካልተመለሱ ድረስ በማያምኑና በግብዞች ላይ የእግዚአብሔር የዘላለም ፍርድ ይኖራል።

በዚህም ምስክርነት አማካይነት በዚህ ሕይወትና በሚመጣው ሕይወት እግዚአብሔር ይፈርዳል።(1)

(1)ኢሳ 58÷1፤ ማቴ 16÷19፤ ዩሐ 3÷31-36፤ 8÷24፤ 20÷21-23፤ ሐሥ 10÷43፤ 2ቆሮ 2÷15-16።

85. በክርስቶስ ትእዛዝ መሠረት፤ ክርስቲያን ነኝ እያሉ በኑሮአቸው ወይም በሕይወታቸው እንደሚገባቸው ሆነው ካልተገኙ፣ ከብዙ ምክርም በኃላ ከከፉ መንገዳቸው ካልተመለሱ፣ ለቤተክርስቲያን ወይም ለቤተክርስቲያን ባለስልጣናት ይጠላለፋሉ።(1) እነርሱም ካልሰሙ፣ ቅዱስምሥጢራትን እንዳይካፈሉ ይደረጋሉ፣ ከክርስትና ሕብረትም ይወገዳሉ፤ በእግዚአብሔር በራሱም ከክርስቶስ መንግስት ይወገዳሉ። ነገር ግን ከጥፋታቸው እንደሚመለሱ ቃል ከገቡና እውነተኛ ለውጥኝ ካሳዩ፣ ወደ ክርስቶስና ወደ በተ ክርስቲያን በአባልነት ዳግመኛ ተቀባይነትን ያገኛሉ።(2)

(1)ማቴ 18÷15-20፤ (2)ሉቃስ 15÷20-24፤ 1ቆሮ 5÷3-5፣ 11-13፤ 2ቆሮ 2÷6-11፤ 2ተሰ 3÷3÷14-15፤2ዩሐ10-11።

ክፍል ሦስት

ምስጋና

32ኛው ሰንበት

86. በጸጋው እንጂ በስራችን ሳይሆን፣ በክርስቶስ አማካይነት፣ ከመከራችን ከተዋጀን፣ ለምን ጥሩ ሥራ መሥራት አለብን?

ምክንያቱም ክርስቶስ በደሙ ከዋጀን በኃላ በህይወታችን ሙሉ ስለ በተከት ለእግዚአብሔር ምስጋና እንድናቀርብ፣(1)

እርሱም በእኛ በኩል እንዲከበር፣(2) እኛም ራሳችን በምናሳየው ፍሬ እምነታችንን እንድንመልስ፣ (4) ሕይወታችንን በመንፈስ ቅዱስ የርሱን መልክ እንዲመስል ያድሳል።

(1)ሮሜ6÷13፤ 12÷1-2፤ 1ቆሮ 6÷20፤ 1ጴጥ 2÷5-10።(2) ማቴ5÷16፤ 1ቆሮ 6÷19-20፤ 1ጴጥ 2÷12።(3) ማቴ 7÷17-18፤ ገላ 5÷6፤ 22-24፤ 2ጴጥ 1÷10-11።(4) ማቴ 5÷14-16፤ ሮሜ 14÷17-19፤ 1ጴጥ 2÷12፤ 3÷1-2፤ 2ጴጥ 1÷10

87. ከምስጋና ቢስነታቸውና ንስሐ ካልገባ ሕይወታቸውን ወደ እግዚአብሔር የማይመለሱ ሊድኑ አይችሉም ማለት ነው?

አዎ፤ በፍጹም ሊድኑ አይችሉም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ርኩሶች፣ጣኦትን የሚያመልኩ፣ሌቦች፣የሚመኙ፣ሰካራሞች፣ ሐሜተኞች፣ ወንበዴዎች፣ እነዚህንም የሚመስሉ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም።(1)

(1) 1ቆሮ 6፡9-10፣ ገላ 5፡19-21፣ ኤፌ 5፡5-6፣ 1ዮሐ 3፡14-15።

33ኛው ሰንበት

88. እውነተኛ ንስሐ ወይም መመለስ በምን በምን ይገለጣል?

በሁለት መንገዶች፣ የአሮጌው ሰው መሞት፣ በአዲሱ ሰው በሕይወት በመኖር።(1)

(1) ሮሜ 6፡4-6፣ 1ቆሮ 5፡7፣ 2ቆሮ 5፡17፣ ኤፌ 4፡22-24፣ ቆላ 3፡5-10።

89. የአሮጌው ሰው መሞት ምንድ ነው?

ስለ ኃጢአት ከልብ የሆነ ኃዘን ኃጢአትን እንድንጠላ አድርጎን፣ ከኃጢአት ዕለት በዕለት እየራቅን መሄድ ነው።(1)

(1)መዝ 51፡3-4፣ 17፣ኢዮኤል 2፡12-13፣ ሮሜ 8፡12-13፣ 2ቆሮ 7፡10።

90. የአዲሱ ሕይወት በሕይወት መኖር ምንድ ነው?

በክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር የምናገኘው ከልብ የሆነ ደስታ (1) እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በጥሩ ስራ መኖራችን ደስ እንዲያሰኘን ማድረጉ ነው።(2)

(1) መዝ 51፡8፣ 12፣ ኢሳ 57፡15፣ ሮሜ 5፡1፣ 14፡17።(2) ሮሜ 6፡10፣ 7፡22፣ 8፡10-11፣ ገላ 2፡20።

91. ጥሩ ስራ ምንድ ነው?

ጥሩ ስራ የሚባለው እንደራሳችን ፍላጎትና ፈቃድ ወይም እንደ ሰዎች ትእዛዝ የሚሰራ ሳሆን፣ ከእውነተኛ እምነት እየመነጨ፣(1) ለእግዚአብሔር ክብርማ እንደ እግዚአብሔር ሕግ ሲፈጸም ብቻ ነው።

(1) ዮሐ 15፡5፣ ሮሜ 14፡23፣ ዕብ 11፡6።(2) ዘሌ 18፡4፣ ሳሙ 15፡22፣ ኤፌ 2፡10።(3) 1ቆሮ 10፡31። (4) ዘዳ 12፡32፣ ኢሳ 29፡13፣ ሕዝ 20፡18፣ 20።(5) ዘኁ 15፡39፣ ማቴ 15፡7-9።

አስርቱ ትእዛዛት

34ኛው ሰንበት

92. የእግዚአብሔር ትእዛዝ ምንድ ነው?

አንደኛው ትእዛዝ። እግዚአብሔርም ይህን ሁሉ ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር በሰማይ ካለው፣ በታችም በምድር ካለው፣ ከምድርም በታች በውሃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፣ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውምም፣ በሚጠሉኝ እስከ ሶስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማድረግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና።

ሶስተኛ ትእዛዝ

የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፣ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና።

አራተኛው ትእዛዝ

የሰንበት ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ስራ ተግባርህን ሁሉ አድርግ፣ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው፣ አንተ ወንድ ልጅህም፣ ሴት ልጅህም፣ ሎሌህም፣ ገረድህም፣ ከብትህም፣ ከደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ስራ አትስሩ፣እግዚአብሔርበስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፣ ባህርንም ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ ባርኮታል ቀድሶታልምና።

አምስተኛው ትእዛዝ አባትህንና እናትህን አክብር፣ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም ስድስተኛው ትእዛዝ አትግደል ሰባተኛው ትእዛዝ አታመንዝር።

ስምንተኛው ትእዛዝ አትስረቅ

ዘጠነኛው ትእዛዝ በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር አስረኛው ትእዛዝ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም፣ ገረዱንም፣ በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።(1) ዘፀ 20፡1-17 ዘዳ 5፡6-21

93. ትእዛዙን እንዴትሊከፍሉ ይችላሉ?

በሁለት ይከፈላሉ አንደኛው ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት ያስተምረናል ሁለተኛው ለባልንጀራችን ልናደርግ ስለሚገባን ነገሮች(1)

(1) ማቴ 22፡37-40

94. ጌታ በመጀመሪያው ትእዛዝ ምን እንደሆነ ጠየቀ?

ለደህንነቱ ስል የጣኦት አምልኮን እንዳስወግድና እንድንርቅ (1) ጥንቆላ ባዕድ አምልኮ (2) ወደ ፍጡራንና ወደ ቅዱሳን የሚደረግ ጸሎት (3) ሲብራራም እውነተኛውን እግዚአብሔር ወደ ማወቅ እንደመጣ (4) በእርሱ ብቻ እንድንታመን (5) በሙሉ ትህትና ዝቅ እንድንል (6)፣ እንድንታገስ (7)፣ መልካምን ከእርሱ ብቻ እንዳገኝ (8)፣ ፍቅር (9)፣ ፍርሃት (10) እናም በሙሉ ልቤ እንድናከብረው (11) በጥቅሉ ከእርሱ ፈቃድ ተቃረኑትን ነገሮች ሁሉ ፍጥረታትንና አነስተኛ ተግባራትን ማስወገድ።(12)

(1) ቆሮ 6፡9-10 10፡5-14 1ዮሐ 5፡21 (2) ዘሌ 19፡31 ዘዳ 18፡9-12 (3)ማቴ 4፡10 ራዕ 19፡10 22፡8-9 (4) ዮሐ 17፡3፣5. ኤር 17፡5፣ 7 (6)1 ጴጥ 5፡5-7 (7)ሮሜ 5፡3-4 1ቆሮ 10-10 ፊሊ 2፡14 ቆላ 1፡11 ዕብ 10፡36 (8)መዝ. ዳዊት 104፡27-28 ኢሳ 45፡7 ያዕ 1፡ 17 (9)ዘዳ 6፡5 (ማቴ 22፡37) (10)ዘዳ 6፡2 መዝ 111፡10 ምሳ 1፡ 7፣9፣10 ማቴ 10፡28፣1 ጴጥ 1፡17 (11) ዘዳ 6፡13 ማቴ 4፡10 ዘዳ 10፡20 (12) ማቴ 5፡29፣3010፡37-39 ሐሥ 5፡29

95. የጣኦት አምልኮ ምንድ ነው?

የኣኦት አምልኮ በእውነተኛው እግዚአብሔር ምትክ ወደ ሆነ ነገር ማዘንበልና መታመን ማለት ነው። ይህም በእርሱ ቃል ራሱን እንዳጋለጠው ነው። (1)

(1) 1 ዜና 16፡26 ገላ 4፡8-9 ኤፌ 5፡5 ፊል 3፡19 1 ቆሮ 11፡24-26

ሁለተኛው ትዕዛዝ

35ኛው ሰንበት

96. በሁለተኛው ትዕዛዝ እግዚአብሔር የሚያዘው ምንድ ነው?

በምንም አይነት እግዚአብሔርን መልክ እንዳንስል ይከላከላል፣ (1) ወይም በተሳለው ስዕል አማካይነት እንዳናመልከው ወይም እርሱ ካዘዘው ውጭ በምንም አይነት መንገድ እንዳናመልከው ይከላከላል። (2)

(1) ዘዳ 4፡15-19፣ ኢሳ 40፡18-25፣ ሐሥ 17፡29፣ ሮሜ 1፡22-24። (2) ዘኃ 10፡1-7፣ ዘዳ 4፡23-24፣ 12፡30-32፣ 1ሳሙ 15፡22-23፣ ማቴ 15፡9፣ ዮሐ 4፡23-24።

97. እንግዲህ ይህ ማለት የምንም አይነት ምስል መሳል እንችልም ማለት ነውን?

እግዚአብሔር በምንም አይነት መንገድ በምስል ሊገለጥ አይችልም። ፍጡራን ግን በስዕል መገለጥ ይችላሉ፣ ነገር ግን እነዚህን ምስሎች ለማምለኪያ ወይም እግዚአብሔርን ለማገልገያ ልናደርጋቸው አይገባንም።(1)

(1) ዘጸ 23፡24-25፣ 34፡13-14፣ 17፣ ዘኁ 33፡52፣ዘዳ 7፡5፣ 12፡3፣16፡22፣ 2ነገ 18፡4-5፣ ኢሳ 40፡4-5፣ ኢሳ 40፡25፣ ዮሐ 1፡18።

98. ይሁን እንጂ፣ ሥዕሎች በቤተ ክርስቲያን ውስይ ለሕዝቡ እንደ መጽሐፍ ማስተማሪያ ሆነው ሊፈቅዱ አይገባምን?

በፍፁም። ከእግዚአብሔር በልጠን ብልህ ለመሆን መሞከር የለብንም። እርሱ በማይናገሩ ምስሎች ሕዝቡን ለማስተማር አልመረጡም።(1) ነገር ግን እርሱ ሕዝቡን ሊያስተምር የመረጠው ሕያው በሆነ የቃሉ ስብከት ነው። (2) (1) መዝ 135፡15-18፣ ኤር 10፡8፣ ዕብ 2፡18-20።(2) ሮሜ 10፡14-17፣ 2ጢሞ 3፡16-17 ጴጥ 1፡19።

ሶስተኛው ትእዛዝ

36ተኛው ሰንበት

99. በሶስተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር የሚያዘው ምንድ ነው?

በመራገም፣(1) ወይም በሐሰት በመማል፣ (2) ወይም በማያስፈልጉ መሐላዎች የእግዚአብሄርን ስም በከንቱ በመጥራት ማርከስ የለብንም። ወይም በሐሰት እነዚህን መጥፎ በደሎች ሌሎች ሲፈጽሙ እያየንና እየሰማን በዝምታችን እንደተስማማን ሆነን መገኘት የለብንም፣ (4) ባጠቃላይ የተወደሰውን የእግዚአብሔር ስም በፍርሃትና በማክበር ባልሆኑ መንገዶች መጠቀም፣(5) በአንጻሩም፣ በትክክለኛው የስሙ

አጠራራችን ሌሎች ስሙን እንዲያከብሩት፣ (6) እንዲያመልኩ፣ ማድረግ እንዳለብን ያዘናል።(7) በንግግራችን ሁሉ እና በስራችን ሁሉ እርሱን ማክበር አለብን።(8)

ዘሌ 24፡10-17።(2) ዘሌ 19፡12።(3) ማቴ 5፡37፣ ያዕ 5፡12። (4)ዘሌ 5፡1፣ ምሳሌ 29፡24።(5) መዝ 99፡1-5፣ኢሳ 45፡23፣ኤር 4፡2።(6) ማቴ 10፡32-33፣ ሮሜ 10፡9-10።(7)መዝ 50፡14-15፣ 1ጢሞ 2፡8።(8) ሮሜ 2፡24፣ ቆላ 3፡16-17፣ ጢሞ 6፡1፣1ጴጥ 3፡ 15።

100. በመሓላ በርግማን የእግዚአብሔር ስም ማርከስ ምን ያክል ከፍ ያለ በደል ቢሆን እነዚህን ነገሮች የሚፈጽሙትን በተቻለ መጠን ለመከላከል በማይጥሩትም ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ የሚገለጠው?

አዎ፣ በርግጥም በላይ ስለሚያስቆጣው ነው (1) ስሙን በከንቱ የሚጠሩት በሞት እንኳ እንዲቀጡ ያዘዘው።(2)

(1) ዘሌ 5፡1።(2) ዘሌ 19፡2፣ 24፡15-16፣ ምሳ 29፡24-25።

37ተኛው ሰንበት

101. ለመሆነ በአክብሮት መንገድ በእግዚአብሔር ስም መማል ተፈቅዷልን?

አዎ፣ ባለስልጣን በሚያዙት ጊዜ ወይም አስፈላጊ በሆነ ወቅት ታማኝነትንና እውነተኛነትን ለመመስረትና ለማሳወቅ ለእግዚአብሔር ክብር ሲባልና ሌሎችን ለመጥቀም ሲባል መማል በእግዚአብሔር ቃል ተደግፏል፣ (1) ስለሆነም በብሉይ ኪዳን ቅዱሳንና በአዲስ ኪዳን ቅዱሳን በትክክለኛ መንገድ በተግባር ላይ ውሏል።(2)

(1)ዘዳ 6፡13፣ 10፡20፣ ኢሳ 48፡1፣ ኤር 4፡1-2፣ዕብ 6፡16።(2) ዘፍ 21፡24፣31፡53-54፣ ኢያሱ 9፡15፣ 19፡15፣19 1ሳሙ 24፡22፣ 1ነገ 1፡29-30፣ ሮሜ 1፡9፣ 2ቆሮ 1፡23።

102.በፍጹም ትክክለኛው መሀላ የሚፈጸመው?

በእግዚአብሔር ስም ብቻ ነው፣ ምክንያቱም እርሱ ብቻ ልብን የሚመረምር ስለሆነ እውነት የምንናገር ለመሆናችን መመስከር ይችላል፣እውነትንም ካልተናገርን ይቀጣናል፣(1) ይህ አይነት ክብር ለማንም ፍጡር ሊሰጥ አይገባም።

(1)ሮሜ 9፡1፣ 2ቆሮ 1፡23።(2) ኤር 5፡7፣ ኢሳ 65፡16፣ ማቴ 5፡34-37፣ 23፡16-22፣ዕብ 5፡12።

አራተኛው ትእዛዝ
38ተኛው ሰንበት

103. በአራተኛው ትእዛዝ እግዚአብሔር የሚያዘው ምንድ ነው?

በመጀመሪያ፣ የወንጌል አገልግሎትና የወንጌል ትምህርት ቤቶች እንዲካዱ እግዚአብሔር ይፈልጋል፣(1) እኔም፣ በተለይም በእረፍት ቀን፣ በትጋት ቤተክርስቲያን መሄድ እንዳለብኝ፣(2) ያም የእግዚአብሔርን ቃል እማር ዘንድ፣(3) ቅዱስ ሚስጥራትን እቀበል ዘንድ፣(4) በይፋ የእግዚአብሔርን ስም እጠራ ዘንድ፣(5) ክርስቲያናዊ ቸርነት እሰጥ ዘንድ፣(6) በሁለተኛ ደረጃ፣ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ከክፋት ስራዎቼ አርፍ ዘንድ፣ ጌታ በመንፈስ ቅዱስ በህይወቴ እንዲሰራ ፈቃደኛ እንድሆንና ገና በዚህ ህይወት ሳለሁ ዘላለማዊውን ሰንበት እጀምር ዘንድ ነው።(7)

(1)ዘዳ 6፡4-9፣20-25፣ 1ቆሮ 9፡13-14፣ 1ጢሞ 2፡2፣ 3፡13-17፤ 4፡13-14፤ 5፡17 ቲቶ 1፡5። (2) ዘዳ 12፡12፡5-7፤ መዝ 40፡99-11፤ 69፡26፤ ሐሥ 2፡42-47፤ 2ጢሞ 2፡2፤ 15፤ ዕብ33። (5) 1ቆሮ 14፡16፤ ቆላ 3፡16፤ 1ጢሞ 2፡1-2፤ 8-10። (6) መዝ 50፡14፤ 1ቆሮ 16፡2፤ 2ቆሮ 8፡9። (7) ኢሳ 66፡23፤ ሐሥ 20፡7፤ ገላ 6፡6፤ ዕብ 4፡9-11።

አምስተኛው ትእዛዝ
39ተኛው ሰንበት

104. አምስተኛ ትዕዛዝ እግዚአብሔር የሚያዘው ምንድነው?

ለአባቴና ለእናቴ፤ እንዲሁም በእኔ ላይ ሥልጣን ላላቸው ሁሉ ክብር፣ ፍቅርና ታማኝነትን አሳይ ዘንድ፣ ለሚሰጡኝ ምክርና እርማት በአክብሮትና በትህትና ራሴን እንዳስገዛ፣ በእጃቸው ያስተዳድሩን ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና፣ ድካማቸውን ሁሉ እንድታገስ ያዘኛል።(3)

(1)ዘፍ 9÷24-25፤ ዘጸ 21÷17፤ ምሳሌ 1÷8-9፤ 4÷1፤ 15÷20፤ 20÷20፤ ኤፌ 6÷1-6፣ 22፣ ቆ3÷18፣ 20÷24።

(2) ማቴ 22÷21፤ ሮሜ13÷24፤ ኤፌ 6÷4፣ 9፣ ቆላ 3÷19፣ 21፣ 1ጢሞ 2÷1-2፣ 5÷17፣ ዕብ 13÷17-18።

ስድስተኛው ትዕዛዝ

40ኛው ሰንበት

105. በስድስተኛው ትዕዛዝ እግዚአብሔር የሚያዘው ምንድነው?

ራሴም ሆንኩ በሌላ ሰው አማካኝነት፣ እንኳን በድርጊት ቀርቶ በሃሳም ቢሆን በመቃጣት፣ ባልንጀራዬን እንዳላጣ፣ እንዳልሰድብ፣ እንዳልገድል፣ (1) የበቀል ሃሳብን ሁሉ ራሴንም ለአደጋ እንዳላጋልጥ ያዘኛል።(3) መግደልን ይቆጣጠር ዘንድ ነው መንግስት ራሱ ሰይፍን የታጠቀው።(4)

(1)ዘፍ 9÷6፤ ዘሌ 19÷17-18፤ ማቴ 5÷21-22፤ 26÷52።

(2)ምሳሌ 25÷21፤ ማቴ 5÷25 15÷35፤ ሮሜ 1÷19፤ 12÷19፤ ኤፌ 4÷26።

(3)ማቴ 4÷7፤ 26÷52፤ ሮሜ 13÷11-14፤ ቆላ 2÷23።(4)ዘፍ 9÷6፤ ዘጸ 2114፤ ማቴ 186-7 ሮሜ 13÷4።

106. ይህ ትእዛዝ የሚገረው ስለ መግደል ብቻ ነውን?

አይደለም። እግዚአብሔር መግደል በመከልከሉ የመግደል ሥር የሆነውን ራሱን ቅንዓትን፣ (1) ጥላቻን፣ (2) ቁጣን፣ (3) የመቀበልን ፍላጎት፤ እነዚህ ሁሉ ድብቅ ግድያዎች ስለሆኑ ተከልክለዋል።

(1)ሮሜ 1÷28-32። (2) 1ዩሐ 3÷15፤ ያዕ 1÷19፣ 3÷16።

107. ባልንጀራችንን እንዳንገድል ብቻ ነው የታዘዝነው?

አይደለም። ቅንዓትን፣ ጥላቻንና ቁጣን በመኮነኑ፣ እግዚአብሔር ባልንጀራህን እደራሳችን እንድነወድ ያዘናል፤ (1) ትዕግስትን፣ ሰላምን፣ ትህትናን፣(2) ምሕረትን፣(3) ቸርነትን፣ (4)ለባልንጀራችን እንድናሳየውና ራሱን እንዳይጎዳ በተቻለን መጠን እንድንከላከልለት፣ (5) ለጠላቶቻችን ሳይቀር በጎ እንድናገርግ ያዘናል።(6)

(1)ማቴ 7÷12፤ 22÷39፤ ሮሜ 12÷10። (2) ሮሜ 12÷18 ገላ 6÷1-2፤ ኤፌ 4÷2።(3) ማቴ 5÷7፤ ሉቃስ 6÷36።(4) ሮሜ 12÷10። (5) ዘጸ 23÷5።(6) ማቴ 5÷9 44-45፣ ሮሜ 12÷20-21፤ ቆላ 3÷12-14

ሰባተኛው ትዕዛዝ
41ኛ ሰንበት

108. ሰባተኛው ትዕዛዝ ምን ያስተምረናል?

የምንዝርና ርኩሰት በእግዚአብሔር የተረገመ እንደሆነ፣ (1) ስለሆነም በሙሉ ልባችን ልንፀየፈው እንደሚገባን፤(2) ያገባን ቢሆንም ያላገባን፤ በንፅህና ራስን በመግዛት እንድኖር ያስተምረናል። (4እና3)

(1)ዘኁ 18÷27-30፤ ኤፌ 5÷3-5።(2) ይሁዳ2 22-23።(3) ተሰ 4÷3-8። (4) 1ቆሮ 7÷1-9፤ ዕብ 13÷4።

109. እግዚአብሔር በዚህ ትዕዛዝ የሚከለክላቸው ግልጥ የሆኑትን እንደ ምንዝርና ያሉትን ሀጢአቶች ብቻ ነውን?

ሥጋችንም ነፍሳችንም የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ስለሆኑ፤ ሁለቱንም ንጹህና ቅዱስ አድርገን እንድንጠብቅ ፈቃዱ ነው። ስለሆነም፣ ንጹህ ያልሆኑ ድርጊቶችን፣ ጥቅሻዎችን፣ ቃላትን(1)፣ሐሳብን፣ ፍላጎትንና(2)፤ ስሜቱን ቀስቃሽ ከሆኑ ነገሮች ሁሉ እንድንርቅ እግዚአብሔር ይከለክለናል።

(1)1ቆሮ 6÷18-20፤ ኤፌ 5÷3-4።(2) ማቴ 5÷27-30።(3) 1ቆሮ 15÷33፤ ኤፌ 5÷18-19

ስምንተኛው ትዕዛዝ
42ኛ ሰንበት

110. እግዚአብሔር በስምንተኛው ትዕዛዝ የሚከለክለው ምንድን ነው?

እግዚአብሄር የሚከለክለው ይህም መሰሎቹን በመንግስት ህግጋት የሚቀጡትን ስርቆትንና(1) ዘረፋን (2) ብቻ ሳይሆን፣በክፉ ማታለልና ዘዴ፣ወይም ሀይል በመጠቀም የሌላውን ሀብት ለመውሰድ መሞከርን(3) ፣አታላይ ሚዛኖችን(4) መለኪያዎችን (5) ናቸው ተብለው ሆነው የማይገኙ እቃዎችን፣ወለድን(6) እንዲሁም በእግዚአብሄር የተከለከሉ ማንኛውም አይነት ምኞቶችን (7) ፣እግዚአብሄር የሰጠንን ስጦታዎች በታቀደላቸው መሰረት በአግባቡ አለመጠቀምን(8) ጭምር እግዚአብሄር በስምንተኛው ትእዛዝ ይከለክላል።

(1)1ቆሮ 6፡10፡፡(2) ዘፀ 22÷1፤1ቆሮ 5÷9-10፣6÷9-10፣6÷9-10፡፡(3) ሚክ 6÷10፤ኤፌ5÷5፡፡(8) ምሴ 5÷10፣21÷20፤ 23÷20-21፤ሉቃስ 16÷10-13 ዮሐ 6÷12 1ጢሞ 6÷10

111. እግዚአብሄር በዚህ ትእዛዝ ካንተ ምን ይፈልጋል? የባልንጀራህን ሀብት በምትችለው መጠን እንድንከባከብ፣ እንዲሁም ሌሎች ለኔ ያደርጉልኝ እንደምፈልገው ላደርግለት(1) ፣በታማኝነት እየሰራሁ ችግረኞችን እረዳ ዘንድም (2) በዚህ ትእዛዝ እግዚአብሄር በተጨማሪ ያዘኛል፡፡

(1) ማቴ 7÷12 (2) ዘፍ 3÷19ኢሳ 58÷5-10 ገላ6÷9-10 ኤፌ 4÷28 ፌል 2÷4 1ጢሞ 6÷6-7

ዘጠነኛው ትእዛዝ
43ኛው ሰንበት

112. በዘጠነኛው ትእዛዝ እግዚአብሄር የሚያዘው ምንድን ነው? በማንም ላይ በሀሰት እንዳንመሰክር(1)፣የማንንም ቃል ላልጠመዝዝ (2) ሀምተኛና ስም አጥፊ እንዳንሆን(3)፣ ስለራሱ ባንመሰክርም በማንም ላይ በእኮላ ላልፈርድ (4) ነገር ግን እግዚአብሄርም ከባድ ቁጣ ፈርቼ የራሱን የሴይጣን ስራ እንደሆኑ ቆጥሬ ውሸትንና ማታለልን እንዳስወግድ (5 እና 6)፣ ፍርዱንና ፍትህን በተመለከተና በሌሎች ጉዳዮች ላይ እውነትን ልወድ ፣ እውነት ልናገር (7) ፣ እንዲሁም በምችለው መንገድ የባልንጀራዬን መልካም ስም እንድንከባከብና እንድጠብቅታዝዣለሁ፡፡

(1) ምሳሌ 19÷5-9 (2) መዝ 15÷3 (3) ሮሜ÷28-30(4) ማቴ 7÷1-2 ሉቃስ 6÷37(5) ዮሐ 8÷44 (6) ምሳሌ 1÷22፤13÷5(7)

(2) 1ቆሮ 13፡6፣ ኤፌ 4፡25 (8) ዮሐ 7፡21-51 ቆላ 4፡6፣ 1ጴጥ 2፡21፣23፣ 3፡9፣4፡8

አሥረኛው ትእዛዝ
44ኛው ሰንበት

113. በአስረኛው ትእዛዝ እግዚአብሄር የሚያዘው ምንድ ነው?

በምንም አይነት ማንኛውም አይነት ዝንባሌም ሆነ ሀሳብ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመቃወም በልባችን መገኘት የለበትም፣ ነገር ግን ሁል ግዜ ኃጢአትን ከልባችን ልንጠላና በጽድቅ ደስተኞች ልንሆን ይገባል።(1)

(1)መዝ 19፡7-14፣ 139፡23-24፣ ምሳሌ 4፡23 ማቴ 15፡11 19-20ሮሜ 7፡7-8 ያዕ 1፡14-15

114. ወደ እግዚአብሔር የተመለሱ እነዚህን ትእዛዝ በፍጹምነት ሊጠብቋቸው ይችላሉን?

አይችሉም። በዚህ ሕይወት እስካ ድረስ ከሁሉም በልጠው ቅዱስ የሆኑ እንኳ ቢሆን ለመታዘዝ ትንሽ ርምጃ ብቻ ጀምረዋል፣(1) ሆኖም ከትእዛዛቱ አንዳንዶችን ብቻ ለመጠበቅ ሳይሆን የእግዚአብሄርን ትእዛዛት በሙሉ ለመጠበቅ ልባዊ የሆነ ጥረትን ያደርጋሉ።(1) መክብብ 7፡20፣ ሮሜ 7፡14-15 1ቆሮ 13፡9 ዮሐ 1፡8-10 (2)ኢዮብ 9፡2-3 መዝ 1፡1-2 19፡13 ሮሜ 7፡22-25 ፊል 3፡12-16 ያዕ 2፡10-11

115. በዚህ ሕይወት እስካለ ድረስ ማንም ሊጠብቃቸው ካልቻለ ታዲያ ለምንድነው እግዚአብሔር አስርቱ ትእዛዛት የጫነብን?

በመጀመሪያ ደረጃ በሕይወት እስካለ ድረስ ስለ ኃጢአት ባህርያችን በበለጠ እንድንረዳ፣ ስለዚህም በበለጠ ትጋት የኃጢአት ይቅርታንና ጻድቅን ለክርስቶስ እንሻ ዘንድ (1) ሁለተኛ ከዚህ ሕይወት በኃላ ብጽእናን እስክጎናጸፍ ድረስ፣ ከደረጃ ወደ ደረጃ ወደ እግዚአብሔር መልክ እንለወጥ ዘንድ ያለ ማቋረጥ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ከእግዚአብሔር በትጋት እንድንጠይቅ እግዚአብሔር አስርቱ ትእዛዛትን ሰጥቶናል።(2)

(1)መዝ. 32፡5፣ ሮሜ.3፡19-26፣ 7፡7፣24-25፣ 1ዮሐ. 1፡9 (2) 1ቆሮ 9፡24፣ ፊል 3፡12-14፣ 1ዮሐ. 3፡1-3

45ኛው ሰንበት

116. ጸሎት ለክርስቲያን ለምን አስፈላጊ ሆነ?

እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምስጋና የፀሎት ታላቁ ክፍል ስለሆነና(1) እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን ፀጋ የሚሰጠው ያለማቋረጥና ከልቡ ለሚለምኑት ብቻ ስለሆነና

እነርሱም ለሚቀበሉት ጸጋ ምስጋና ለእርሱ ስለሚያቀርቡት ነው፡ ፡(2)
(1)መዝ 50፡14-15 116፡12-19 ተሰ 5፡16-18 (2)ማቴ 7፡7-8 13፡12 ሉቃስ 11፡9-13 ኤፌ 6፡18፡፡
117. በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለውና እገዚአብሔር የሚሰማው ጸሎት ምን አይነት ነው?
በመጀመሪያ በሙሉ ልባችን(1) ራሱን በቃ የገለጠልንን እውነተኛው የሆነውን አንዱን አምላክ መጥራት፣ (2) እንድጠይቀው ላዘዘን ነገሮች ሁሉ መጸለይ (3) ሁለተኛው የሚያስፈልገንንና ከንቱነታችንን በትክክል አውቀን በመለኮታዊ ክብሩ ፊት ራሳችንን ማዋረድ (4) ሶስተኛው ምንም እንኳ እና የማንገባ ብንሆንም፣ ለጌታችን ለክርስቶ ሲል ጸሎታችንን በርግጥ እንደሚሰማ እርግጠኛ መሆንመ (5፣6 እና 7) ይህም በቃ በሰጠው የተስፋ ቃል መሰረት ነው(8)
(1)ዮሐ 4፡22-24 (2ያ፣ ሮሜ 8፡26 1ሐ 5፡14(3) መዝ 2፡8(4) 2ዜና 20፡12 (5) መዝ 2፡10 3፡18 ኢሳ፡2(6) ሮሜ 1፡14 ያዕ 1፡ 6 (7) ዳን 9፡17-18 ዮሐ 14፡13-16 (8) መዝ 143፡1 ማቴ 7፡8 ሉቃስ፡13፡፡
118. እግዚአብሔር እንድጠይቀው ያዘዘን ምንድን ነው?
ለነፍሳችንንና ለስጋችን(1) የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ እንድንለምነው አዞናል፡፡ ህም ልመና ጌታችን ክርስቶስ ባስተማረን ጸሎት ላይ ተጠቃሏል፡፡
(1)ማቴ 6፡33 ፊል 4፡6 ያዕ 1፡17 1ጴጥ 5፡7፡፡
119. ጌታችን ያስተማረን ጸሎት ምንድን ነው?
እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፡፡ በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግስትህ ትምጣ ፈቃህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን፣ የዕለት እንጀራችንን ስጠን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተናም አታግባን መንግስት ያንተናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ አሜን፡፡(1) (1)ማቴ 6፡ 9-13 ሉቃ 11፡2-4

46ኛው ሰንበት

120. እግዚአብሔር "አባታችን" ብለን እንድንጠራው ክርስቶ ለምን አዘዘን?

ገና ከጸሎታችን መጀመሪያ ላይ ለጸሎታችን መሰረት የሆነውን ለእግዚአብሔር አክብትና በእግዚአብሔር መቅረብ እንዳለብን ሊያነቃቃን ስለፈለገ ነው። በተጨማሪም እግዚአብሔረው አባታችን ሊሆን የቻለው በክርስቶስ ምክንያት ስለሆነ የምድራዊ ወላጆቻችን እንኳን የማያሳዩንን ርህራሄ አስበልጦ ራርቶልን የለመንነውን ሁሉ በአባትነቱ እንዲሰጠን እንድናምን ነው።(1)

(1)ኢሳ 63÷16 ማቴ 7÷9-11 ሉቃስ 11÷11-13 1ጴጥ 1÷17

121 "በሰማይ የምትኖር የሚለው ተጨመረ"?

የእግዚአብሄርን ሰማያዊ ክብር እንደምድራዊ ክብር እንዳናናየውና (1) ከእርሱ መለኮታዊ ኃይል ለሥጋችንና ለነፍሳችን የሚያስፈልጉን እንድንጠብቅ ነው። (2)

(1) ኤር 23÷23-24፤ሐሥ 17÷24-27። (2) 1ነገ 8÷28፤ መዝ 115÷3፤ ማቴ 6÷25-34 ሮማ 8÷10፣12፣31-32

47ኛው ሰንበት

122. የመጀመሪያው ልመና ምንድነው?

"ስምህ ይቀደስ"፣ ይህም ማለት በመጀመሪያ አንተን በትክክል እንድናውቅህ እውቀት ስጠን፣(1) እንድንቀድስህም፣ ከፍ ከፍ እንድናደርግህ፣ ኃይልህ፣ በጎነትህ፣ ፍርድህ፣ ምህረትህ፣ እና እውነትህ እንዲያበራ ስለስራህ ሁሉ እንድናወድስህ፣(2) ሕይወታችንን በሙሉ ማለትም፣ ሓሳባችንን፣ ቃላችንን፣ ተግባረሰችንን፣ያንተን ስም በሚያሰድብ ሳይሆን፣ አንተን በሚያከብር መንገድ እንድንመራ ማለት።(3)

(1)መዝ 119፡105፣ ኤር 9፡23-24፣ 31፡33-34፣ ማቴ 16፡17፣ ዮሐ 17፡3፣ ያዕ 1፡5።(2) ሉቃስ 1፡46-55፣ 68-75፣ ሮሜ 11፡33-36።(3) መዝ 71፡8፣ 16፣ 92፡1-2፣ 100፡3-4፣ 115፡1፣ ማቴ 5፡16፣ ኤፌ 1፡16-17

48ኛው ሰንበት

123. ሁለተኛው ልመና ምንድነው?

"መንግስት ትምጣ" ማለትም በቃልህና በመንፈስህ ግዛት፣ ራሳችንን ለአንተ ከጊዜ ወደ ጊዜ በበለጠ እንሰጣለን፣(1) ቤተ ክርስቲያንህን ጠብቃት፣ አስፋፋት፣(2) የዲያብሎስን ስራ አፍርስ በአንተ ላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያድርገውን ኃይል ሁሉ ስበር፣ በቅዱስ ቃልህ ላይ የሚነሱትን የክፉውን ወጥመዶች ሁሉ ሰባብር፣(3) ይህም መንግስትህ በሙላት እስክትመጣ ድረስና አንተ ሁሉ በሁሉ እስክትሆን ድረስ።(4)

(1)መዝ 119፡5፣ 105፣ 143፡10፣ ማቴ 6፡33።(2) መዝ 51፡18፣ 122፡6-7፣ ማቴ16፡18፣ ሐሥ 2፡42-47።(3) ሮሜ 16፡20፣ 1ዮሐ 3፡8።(4) ሮሜ 8፡22-23፣ ራእይ 22፡17፣ 20። መዝ 102፡12-13፣ 1ቆሮ 15፡24፣ 28፣ዕብ 12፡28፣ ራእይ 11፡15።

49ኛው ሰንበት

124. ሰስተኛው ልመና ምንድነው?

"ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን"፣ ያም ማለት እኛና የሰው ልጆች በሙሉ ያለመከራከር ብቻውን በጎ ለሆነው ለአንተ ፈቃድ የገፍል ፈቃዳችንን በሙሉ እንድናስገዛ፣(1፣2) እነደዚህም በሰማይ መላዕክት እንደሚታዘዙ፣ እያንዳንዱ የተጠራበት ጥሪ በፈቃደኝነትና በታማኝነት ያገለግል ዘንድ።(3፣4)

(1)ማቴ 16፡24።(2) ማቴ 7፡21፣ 16፡24-26፣ ሉቃስ 22፡42 ሮሜ 12፡2፣ ቲቶ 2፡11-12።(3) 1ቆሮ 7፡17-24፣ ኤፌ 6፡5-9፣ (4) መዝ 103፡20-21፣ ሮሜ 12፡2፣ ዕብ 13፡21።

50ኛው ሰንበት

125. አራተኛው ልመና ምንድነው?

"የእለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን" ማለትም፣ ለስጋችን የሚያስፈልገንን ሁሉ እንድትሰጠን መልካም ፈቃህ ይሁን፣(1)በዚህም አንተ ብቻ የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ እንደሆንህ እንድንገነዘብ፣(2) ያለ አንተም በረከት መጨነቃችንም ሆነ ጥረታችችን፣ ያንተም ስጦታዎች ቢሆኑ ያለ አንተ በረከት ምንም ሊጠቅሙን አይችሉም፣(3) ስለዚህም መተማመናችንን

ከፍጡሮች ላይ አንስተን በአንተ ላይ ብቻ እንድናደርግ ይሁን ማለት ነውው፡(4)

(1)መዝ 104፡27-30፣ 145፡15-16፣ ማቴ 6፡25-34፡፡(2) ሐሥ 14፡17፣17፡25-28፣ ያዕ 1፡17፡፡(3)ዘዳ 8፡3፣መዝ 37፡3-7፣16-17፣ 127፡1-2፣ 1ቆሮ 15፡58፡፡(4) መዝ 55፡22፣ መዝ 62፣ መዝ 146፣ ኤር 17፡1-8፣ ዕብ 13፡5-6፡፡

51ኛው ሰንበት

126. አራተኛው ልመና ምንድነው?

"እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣ በደላችንን ይቅር በለን"፣ ይህም ማለት፣ ከልባችን ባልጀራችንን ይቅር ማለታችን ያልተ ጸጋ በልባችን እንዳለ ማረጋገጫው ስለሆነ፣ ለክርስቶስ ስትል የእኛን የከንቱ ኃጢአተኞች ብዙ በደልና ፈጥኖ የሚጠለንን ኃጢአት አትቁጠርብን ማለት ነው፡፡ (2፡1)

(1)መዝ 51፡1-7፣143፣ ሮሜ 8፡1፣ 1ዮሐ 2፡1-2፡፡(2) መዝ 51፡5-7፣ ማቴ 6፡14-15 18፡21-25፣ ኤፌ 1፡7፡፡

52ኛው ሰንበት

127. ስድስተኛው ልመና ምንድን ነው?

"ከክፉ አድነን እንጂ፣ ወደ ፈተና አታግባን" የሚለው ሲሆን፣ ትርጉምም፣ እኛ በራሳችን እጅግ ደካሞች ስለሆንን፣ ያለማቋረጥ የሚያጠቁንና የሞት መሳሪያዎች ከሆኑት ጠላቶቻችን፣ ከዲያቢሎስ፣(2) ከዓለም፣ (3) እና ከስጋችን (4) ፊት ለአንድ ሴኮንድ እንኳ መቋቋም አንችልም፣(1) ስለዚህ የመጨረሻውን ድላችንን እስክናጎናጽፍ ድረስ(5) በመንፈሳዊ ትግላችን (6) እንድትጠብቀንና እንድታጠነክረን በጎ ፈቃድህ ይን ማለት ነውው፡

መዝ 103፡14-16፣ ዮሐ 15፡1-5፡፡ (2) 2ቆሮ 11፡4፣ ኤፌ 6፡10-13፣ 1ጴጥ 5፡8-9፡፡(3) ዮሐ 15፡18-21፡፡ (4) ሮሜ 7፡23፣ ገላ 5፡17፡፡(5) ማቴ 10፡19-20፣ 26፡41፣ ማር 13፡33፣ ሮሜ 5፡3-5፡፡ (6) 1ቆሮ 10፡13፣ 2ቆሮ 12፡7፣ 1ተሰ 3፡13፣ 5፡23-24፡፡

128. ይህን ፀሎት ስትደመድም ምን ትላለህ?

"መንግስት ያንተ ናትና፣ ኃይል ፣ ክብርም ለዘላለም በማለት ሲሆን፣ ትርጉሙም፣ ይህንን ሁሉ የምንጠይቅህ፣ ንጉሳችን ስለሆንህና በሁሉም ነገሮች ላይ ስልጣን ስላለህ፣ መልካም የሆኑትን ነገሮች ሁሉ ልትሰጠን ፈቃደኛና ችሎታ ያለህ ነህ፣(1) በዚህም የኛ ሳይሆን፣ የአንተ ቅዱስ ስም ይከበር ዘንድ ማለት ነው። (2)

(1) ሮሜ 10፡11-13፣ 2ጴጥ 2፡9 (2)መዝ 115፡1፣ ኤር 33፡ 8-9፣ ዮሐ 14፡13

129. "አሜን" የሚለው ቃል ትርጉም ምንድን ነው?

"አሜን" ማለት በእውነት ይደረግ ይደረጋልም ማለት ነው። እነዚህን በልቤ መፈለጌ እርግጠኛ እንደሆንሁ ሁሉ እግዚአብሔርም ጸሎቴን እንዲሁ በርግጥ ሰምቷል ማለት።

መዝ 145፡18-19፣ ኢሳ 65፡24፣ 2ቆሮ 1፡20፣ 2ጢሞ 2፡13።